

ቅድስት ድንግል ማርያም
ምስለ ፍቁር ወልዳ





ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ
ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም
ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት





## ማውጫ

ገጽ

1. ርዕሰ አንቀጽ ....... 6
2. የቅዱስ ፓትርያርክ መልእክት ....... 10
3. የጠቅላይ ዋና ሥራ አስኪያጅ መልእክት ....... 15
4. የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ መልእክት ....... 21
5. የስ/ወ/ሐ/ተልእኮ መምሪያ ሊቀ ጳጳስ መልእክት ....... 28
6. የስ/ወ/ሐ/ተልእኮ መምሪያ ዋና ሓላፊ መልእክት ....... 33
7. በዓለ ጥምቀት ....... 38
8. ዘመነ መርዓዊ ....... 45
9. የቃና ዘገሊላ ....... 54
10. ልደተ እግዚእ ....... 66

**የመጽሔቱ ዋና አዘጋጅ**
- መጋቤ አእላፍ ኤፍሬም በየነ

**የልዩ ዕትም ዝግጅቱ ዋና ሓላፊ**
- መምህር ማርቆስ ተበቃ

**ተባባሪ አዘጋጅ**
- መምህርት ኑኃሚን ዋቅጅራ

**አርታዒያን**
- መምህር ዘማርያም ጌጡ
- መምህር ሽፈራው እንዳሻው
- መጋቤ ብሉይ አእምሮ ዘውዴ

**ፎቶ ግራፈር፡**
- መልአከ ሰላም አባ ኪሮስ ወልደአብ
- የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሚዲያ

**ዲዛይን ቅንብር**
- ሂሩት ሀብትይመር

**አሳታሚ**
- የስብከተ ወንጌል እና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ

**አታሚ**
- ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት

ርዕሰ አንቀጽ

# አንዲት ጥምቀት

በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምኖ መጠመቅ የክርስትና ሃይማኖት መሠረት የመንግሥተ ሰማያት ቁልፍ መግቢያ በር ነው፡፡

በስመ ሥላሴ ለአማንያን በዕደ ካህናት የምትፈጸም ጥምቀት አንዲት ብቻ ናት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱ ዓለምን አድኖ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ደቀ መዛሙርቱን እጆቹን ዘርግቶ ከባረካቸውና ሥልጣነ ክህነትን ከሰጣቸው በኋላ ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁን ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራ ችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ *(ማቴ. 28፥19- ሉቃ 24፥50)*

ይህንንም መለኮታዊ ትዕዛዝ መሠረት አድርገው ቅዱሳን አበው ሐዋርያት ከቤተ አይሁድና ከጣዖት አምላኪዎች የደረሰባቸውን ግፍና መከራ በመቀበል መራራ ሞትን በመታገስ ወንጌል በማስተማር ጥምቀትን ለአማንያን ፈጽመዋል ቅድስት ቤተክርስቲያንንም ከዓለም መካከል እስከ አጽናፈ ዓለም እንድትደርስ አድርገዋል፡፡

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትዕዛዝ የሆነች በዕደ ሐዋርያት አበው የተፈጸመች አሁንም የምትፈጸም ጥምቀተ ክርስትና አንዲት ብቻ የማትደገም ናት፤

ብርሃነ ዓለም ማኅቶተ ቤተ ክርስቲያን በመባል የሚታወቀው ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ «ወንህነ በአሐዱ» መንፈስ ወበአሐዱ ሥጋ ተጠመቅነ ኵልነ እለሂ አምአይሁድ ወእለሂ እም አረሚ እመኒ ነባሪ ወእመኒ አግዓዚ እስመ ኵልነ አሐደ መንፈሰ ሰተይነ፤ *(1ኛ.ቆሮ 12፥13)*

አይሁድም ብንሆን፣ የግሪክም ሰዎች ብንሆን፣ ባሪያም ብንሆን፣ ገዢም ብንሆን፣ ተጠምቀናል፡፡ ሁላችንም አንድ መንፈስ ጠጥተናል በማለት የክርስቲያኖች ጥምቀት አንዲት መሆኗንና ከየትኛውም ዘርም ሆነ አገር ይሁኑ ክርስቲያኖች በክርስቶስ አንድ መሆናቸውን ያስገነዘባል፡፡ በሌላም በኩል ይህ ታላቅ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ «አሐዱ እግዚአብሔር ወአሐቲ ሃይማኖት ወአሐቲ ጥምቀት ወአሐዱ እግዚአብሔር አብ ለኩሉ ዘላዕለ ኩሉ» *(ኤፌ 4፥5-6)*

በአንድ ተስፋ አንድ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ አንድ ጌታ፣ አንዲት ሃይማኖት፣ አንዲት ጥምቀት፣ ከሁሉ በላይ የሆነ ለሁሉ የሚሠራ በሁሉ የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉ አባት አለ ብሏል፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ጥምቀት አንዲት ናት ያላት ጥምቀት ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማህፀነ ዮርዳኖስ መወለድን ከርጉም ከዲያብሎስ ቁራኙነት ከመርገመ ሥጋ መላቀቅን በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ የምታስገኘው አንዲት ጥምቀት በካህናት እጅ መፈጸም አለባት፡፡

በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ካህኑ ሥርዓተ ጥምቀትን ለመፈጸም ተገቢውን ጸሎት አድርሶ የቀረበውን ውሃ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ሲባርከው ውሃው ተለውጦ በዕለተ ዐርብ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘው ማየ ገቦ ይሆናል፡፡

በዚህ ማየ ገቦ የተጠመቀ ሰው የሥላሴን ልጅነት ያገኛል፤ ከዲያብሎስ ቁራኝነት ከኃጢአት መርገም ይላቀቃል፡፡

በሥልጣነ ክህነት በእደ ካህናት የምትፈጸም ጥምቀት አንዲት ናት ማለት ተጠማቂው ሰው በሊቀ ጳጳስ ቢጠመቅ በካህን ቢጠመቅ በሊቀ ጳጳስ የተጠመቀው በካህኑ ከተጠመቀው አይበልጥም በካህኑ የተጠመቀውም ከሊቀ ጳጳሱ አያንስም ማለት ነው፡፡

ጥምቀት አትደገም አትከለስም አንዲት ናት፤ ሃይማኖትም አትለወጥም አትደገምም ውሉደ ክርስቲያን ወንዶች በተወለዱ በአርባ ቀን ሴቶች በተወለኩ በሰማንያ ቀናቸው ይጠመቃሉ፡፡

ይህም አዳም በተፈጠረ በአርባ ቀኑ ልጅነትን አግኝቶ ገነት ስለገባ ሔዋንም በተፈጠረች በሰማንያ ቀን የልጅነት ጸጋን አግኝታ ገነት ስለገባች ይህ ምሳሌ ተደርጎ ነው አዲስ አማንያን በአመኑበት የእድሜ ዘመን ይጠመቃሉ፡፡ ከዘመነ ብሉይ ጀምሮ በአልምኮተ እግዚብሔር ጸንታ የኖረችው ሀገራችን ኢትዮጵያ ጥምቀተ ክርስትናን የተቀበለችው በዘመነ ሐዋርያት ነበር፡፡

*በግብ.ሐዋ.8፥26-39* በተመዘገበው መሠረት ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ኢየሩሳሌም ሄዶ ቅዱሳት መካናትን ተሳልሞ በሠረገላው ውስጥ መጽሐፈ ኢሳይያስ (ምዕ.53) ሲያነብ ፊልጶስ አግኝቶት፣ የምታነበውን ታውቀዋለህን ሲለው፣ ያለ መምህር ያለ ሰባኪ እንዴት ልረዳ እችላለሁ አለው፤ ፊልጶስም ወንጌልን ሰበከለት፡፡ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባም በክርስቶስ አምላክነት አምኖ፣

**ነዋ ማይ መኑ ይከልአኒ ተጠምቆ** /ውሃ ይኸውና መጠመቅ ማን ይከለክለኛል/ አለ፡፡

ፊልጶስም ከአመንክ ተፈቅዷል አለው፤ ኢትዮጵያዊውም ኢየሱስ ክርስቶስ ወልድ የእግዚብሔር ልጅ መሆኑን አምናለሁ አለ፤ ፊልጶስም ኢትዮጵያዊውን አጠመቀው፤

ስለዚህ ከብሉይ ኪዳን ሐዲስ ኪዳንን የተቀበለች፣ ቅዱሳን ሐዋርያትን እንደ ሌሎች ዓለማት ያላስቸገረች፣ ጣዖት ያላመለከች፣ ኢትዮጵያ ሀገራችን የክርስቲያን ደሴት፣ ሀገረ እግዚአብሔር ትባላለች፡፡

ሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ሊቃውንት በደነገጉት በፍትሐ ነገሥት በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 21 በአንቀጸ ቤተ ክርስቲያን በተደነገገው የሥላሴን ልጅነት ለማግኘት የሚፈጸመው ጥምቀተ ቁርባን ቅዳሴ በመንደር በአዳራሽ አይሁን፤ ታቦተ ሕጉ፣ ሥዕለ አድኅኖ፣ መስቀል ባለበት በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ይሁን፡፡ የተጠመቀውም ሰው በተጠመቀበት ዕለት ይቁረብ ይላል፤

ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ውጭ ጥምቀተ ክርስትና ቅዳሴ የሚፈጽም ካህን ከቤተ ክርስቲያን ይባረር፤ ከክህነቱ ይሻር፤ ይላል፡፡ ጥምቀት ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ ነው፡፡

የቅድስት ቤተ ክርስቲያን የዕለት ከዕለት ሥራዋ ወንጌል መስበክ ማጥምቅ ማቁረብ አምነው የተጠመቁትን አባግዐ ክርስቶስን መጠበቅ ነው፡፡

በየዓመቱ በዓለ ጥምቀት ጥር 11 ቀን ሲከበር ጌታችን ኢየሱስ በእደ ዮሐንስ ለመጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ እንደሄደ ሁሉ ዓመት ሙሉ የተሠለሰበት፣ የተቀደሰበት፣ ጸሎት እጣን ማዕጠንት ያረገበት፣ ታቦተ ሕጉ ከመቅደሱ ወጥቶ ወደ ባሕረ ጥምቀቱ ሲወርድ በታቦቱ ጉዞ ጐዳናው ሠፈሩ ሀገሩ ይባረካል፤ በመንገዱ ሕፃናት ያድጉበታል፤ ሽማግሌዎች ይበረቱበታል፤ ጐልማሶች ይጠነክሩበታል፤ በጠቅላላ ዓመቱን በሙሉ ሰላም ይሰፍንበታል፡፡

ታቦተ ሕጉ ባደረበት ባሕረ ጥምቀት ስብሐተ እግዚአብሔር ደርሶ፣ ቅዳሴ ተቀድሶ፣ አስፈላጊው ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ከተፈጸመ በኋላ ባሕሩ ተባርኮ፣ ሕዝበ ክርስቲያኑ የሚረጨው ውሃ በዓለ ጥምቀትን ለማሰብና ከበረከተ ጥምቀቱ ለመካፈል ነው፡፡

ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቸርነቱና በረከቱ በኋላችን ላይ ይሁን፡፡

# የቅዱስ ፓትርያርክ
# መልእክት



**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ አሜን።**

**‹‹ንሕነኬ ምንተ ንግበር? እኛስ ምን እናድርግ?››**
**(ሉቃ. ፫÷፲፬)**

ይህንን መጠይቃዊ ዐረፍተ ነገር ያቀረቡት በመጥምቁ ዮሐንስ ስብከተ ንስሓ ኅሊናቸው የተነካ ሕዝብ ናቸው። ቅዱስ ዮሐንስ የልዑል እግዚአብሔር መንገድ ጠራጊ ወይም በዘመናችን አገላለጽ÷ የመሲሕ አስተዋዋቂ ሆኖ እንዲያገለግል በእግዚአብሔር የተመደበ

ቅዱስ ሰው ሲሆን፤ ይህ አገልግሎት ከመወለዱ ከሰባት መቶ ዓመታት በፊት በእግዚአብሔር ተነግሮለት ነበር፡፡*( ኢሳ ፵÷፫-፭)*

ከዚህ በኋላም ሲፀነስ በቅዱስ ገብርኤል፥ ሲወለድ ደግሞ በአባቱ በዘካርያስ ይህ አገልግሎቱ ተመስክሮለታል፤ እሱም እኔ መንገድ ጠራጊ ነኝ ብሎ ራሱን ገልጾአል፤ ጌታችንም ይህንኑ አረጋግጦለታል።

ቅዱስ ዮሐንስ የዘመነ ብሉይ መጠናቀቂያ፥ የዘመነ ሐዲስ መጀመሪያ ሆኖ የመሲሑን መምጣት ለማስተዋወቅ በእግዚአብሔር ዘንድ የተመረጠ ነበረና አስተምህሮው የተዋጣለት ነበር፤ ዝናውም በዮርዳኖስ ዙሪያ ባሉ አህጉር ሁሉ ገኖ ነበር።

ሕዝቡም ሁሉ ትምህርቱን ለመስማት፥ ንስሓ ለመግባትና በእሱ ለመጠመቅ እሱ ወዳለበት ፈለገ ዮርዳኖስ ይጐርፉ ነበር።

ከጣዕመ ስብከቱና አስገራሚ ከሆነው የግል ሰብእናው በመነሣት ይመጣል የሚባለው መሲሕ ወይም ክርስቶስ ይህ ሳይሆን አይቀርም የሚል አመለካከት በምድረ እስራኤል በሰፊው መወራት ጀምሮ ነበር።

ይህንን የሰሙ የካህናት አለቆች ሳይቀሩ አንተ ማን ነህ? መሲሑ ነህ? ብለው ዮሐንስን በመልእክተኞቻቸው ጠይቀውት ነበር።

እውነተኛ ትምህርት ከመሲሑ እንደሚገኝ አምነው የእሱን መምጣት ይጠባበቁ ከነበሩትም በጉባኤው ተገኝተው የተለያዩ ጥያቄዎችን አቅርበውለታል፤

እሱም በተሰጠው ጸጋ እግዚአብሔር በትክክል መልሶላቸዋል።

ሰዎች ዮሐንስ መሲሑ ሊሆን ይችላል ብለው ቢገምቱም ዮሐንስ ግን እኔ እሱ (መሲሑ) አይደለሁም፤

እሱ ከእኔ በፊት የነበረ፥ የጫማውን ጠፍር እንኳን መፍታት የማይገባኝ ነው፤ እሱ ከእኔ በኋላ ይመጣል፤ እኔ ከእሱ በፊት መንገድ ጠራጊ ሁኜ የተላክሁ ነኝ በማለት መልስ ይሰጣቸው ነበረ።

የዮሐንስ ጣዕመ ትምህርት በነገረ መለኮት ብቻ ሳይሆን በማኅበራዊ፥ በኢኮኖሚያዊና በመልካም ሥነ-ምግባር ላይ ያነጣጠረ ነበረ።

በዚህ ትምህርቱ ኀሊናቸው የተነካ ሰማዕያን ጥያቄ በማንሣት ‹‹እኛስ ምን እናድርግ?›› እያሉ ይጠይቁት ነበር።

ለጥያቄያቸውም መልስ ሲሰጥ፥ ግብር ለሚሰበስቡ፡- በሕግ ከተቀ መጠው በላይ አብልጣችሁ አታስከፍሉ፤ በደመወዛችሁ ኑሩ እንጂ ጉቦ አትቀበሉ! ብሎ መልሶላቸዋል፤ በጸጥታ ሥራ ለተመደቡ ወታደ ሮችም፡- በኀይላችሁና በጉልበታችሁ ተማምናችሁ በማንም ላይ ግፍ አትሥሩ፤ ማንንም በሐሰት አትክሰሱ ደመወዛችሁ ይበቃችኋል ብሎ አስተምሮአቸዋል፤

የተትረፈረፈ ሀብት ላላቸውም ካላቸው ለሌላቸው በማካፈል እንዲረዱ አዞአቸዋል።

ከዚህም ጋር ሕዝቡ ንስሓ እንዲገቡ፥ በመልካም ሥነ-ምግባር ሕይወታቸውን እንዲመሩ፥ እሱ በውኃ የንስሓ ጥምቀትን የማጥመቅ ሥልጣን ብቻ እንዳለው፥ ከእሱ በፊት የነበረ ከእሱ በኋላ የሚመጣው ክርስቶስ ግን በውኃ፥ በእሳትና በመንፈስ ቅዱስ የማጥመቅ ሥልጣን እንዳለው፤ መሲሑ ዐውድማውን የሚያጠራበት መንሽ በእጁ እንደሆነ፤ ስንዴውን በጎተራ እንደሚያከማች፤ እንክርዳዱን ግን በማይጠፋ እሳት እንደሚቃጥል ከመግለጽ ጋር፤ እነሆ ምሳር በዛፎች ሥር ላይ ተቀምጦአል፤ መልካም

ፍሬ የማያፈራው ሁሉ ይቈረጣል፤ በእሳትም ይቃጠላል እያለ በተራዘመ ስብከቱ ያስተምር ነበር።

ታዲያ በዚህ ጊዜ ነበረ ጌታችን ሊጠመቅ ወደ ዮሐንስ የመጣው።

ጌታችን ዮሐንስን እንዲያጠምቀው በጠየቀው ጊዜ ዮሐንስ፡- እንዴት ይህ ይሆናል? እኔ አንተን የማጥመቅ ብቃት የለኝም ቢልም፥ አጥምቀኝ ተብሎ በጌታችን ስለታዘዘ ለትእዛዙ ተገዢ ሆኖ አጥምቆታል።

ጌታችን ሲጠመቅ በሰው ልጆች ድኅነት ላይ ትልቅ ትርጕም ያላቸው ብዙ መለኮታዊ ድርጊቶች ተገልጠዋል።

እነሱም፡- የሰማይ መከፈት፥ 'ይህ ልጄ ነው' የሚል ከእግዚአ ብሔር አብ ለጌታችን የተሰጠ ምስክርነት፥ የመንፈስ ቅዱስ በነጭ ርግብ አምሳል መውረድና በጌታችን ላይ መቀመጥ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ይህ አምላካዊ ክሥተት እግዚአብሔር ሦስት አካላት ያሉት አንድ አምላክ መሆኑን፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሰውም አምላክም መሆኑን፤ ሰዎች በዚህ አምላካዊ ትምህርትና ክሥተት አምነው ሲጠመቁ የእግዚአብሔር ልጆች፥ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያዎች እንደሚሆኑና ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር ለመግባት በሩ ክፍት እንደሚሆንላቸው የነገሩ ምሥጢረ መልእክት ያሳያል።

እንግዲህ ይህ ሁሉ የሆነው እግዚአብሔር በሰው ላይ ሊፈጽመው የፈለገው አንድ ዐላማና ግብ ስለነበረው ነው፤ እሱም ሰውን ወደ መንግሥቱ መልሶ በማስገባት የዘለዓለም ሕይወትና ክብር እንዲኖረው ማድረግ ነው፤

ይህንን ለማሳካት እግዚአብሔር ይህንን ሁሉ አድርጎአል።

ታዲያ በዚህ ልክ ለወደደን ለእግዚአብሔር ንጹሕ መሥዋዕት ሆኖ የሚቀርብ የእኛ ግብረ መልስስ ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ዋና ተግባራችን ሊሆን አግባብ ነው።

ነገሩን ማስታወስ ስላለብን በየጊዜው እንማረዋለን እንጂ ጥያቄው ተጠይቋል፤ መልሱም ተሰጥቷል። ሆኖም የተሰጠንን መልስ ዛሬም ድረስ ሳንተገብረው እንገኛለን።

እንግዲያውስ ምን እናድርግ ለሚለው ጥያቄ፦ ግብረ ኃጢአትን መሥራት ትተን በዮሐንስ ትምህርት ጸንተን እንኑር ነው መልሱ። ይህ ሕግ በዮሐንስ እንደበት ተነገረ እንጂ ቀዋሚ የሆነ የእግዚአ ብሔር ሕግ ነው።

ከዚህ አኳያ ከእኛ የሚጠበቀው ግብረ መልስ ይህንን ሕግ እያከበርንና እየፈጸምን እሱን በማመንና በመጠመቅ፥ ከእሱ በመወለድ፥ እንዲሁም ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በመቀበልና በመንፈሳዊ ሥነ-ምግባር ሕይወታችንን በመምራት፥ እግዚአብሔር ወዳዘጋጀልንና ወደ ከፈተልን መንግሥተ ሰማያት መግባት ነው።

እግዚአብሔር የተባረከና የተቀደሰ በዓለ ጥምቀት ያድርግልን!
እግዚአብሔር ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!
ወስብሐት ለእግዚአብሔር፤ አሜን።

አባ ማትያስ ቀዳማዊ
ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ሊቀ ጳጳስ ዘአኵስም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

ጥር ፲፩ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም
አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ

# የጠቅላይ ዋና ሥራ አስኪያጅ
# መልእክት



**«ወለደነ በጥምቀቱ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን፤
በጥምቀቱ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ወለደን።»**

**ከሁሉ በፊት እንኳን ለጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን
ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ጥምቀት በሰላም አደረሳችሁ!**

ጥንታዊና ሐዋርያዊ በሆነው በቅድስት ቤተ ክርቲያናችን ሥርዐት መሠረት በየዓመቱ ጥር አሥራ አንድ ቀን የጌታችንና መድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ጥምቀት እናከብራለን፡፡

ጌታችን በዮሐንስ እጅ ለመጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ እንደ ወረደ፥ እኛም ታቦታቱን ከመንበረ ክብራቸው አንሥተን፥ በምስጋና አጅበን፥ ወደ ባሕረ ጥምቀት እንወርዳለን፡፡

በየደረጃው በምናከናውናቸው በሁሉም የበዓሉ አከባበር ሥርዐቶች ውስጥ ጌታችን ለእኛ ያደረገውንና የልጅነታችን መሠረት የሆነውን ነገር እናስባለን፡፡

እርሱ የሁሉ ባለቤት፥ እጸድቅ አይል ጻድቅ፥ ቅዱስና ንጹሐ ባሕርይ የሆነ ጌታ፥ ለእርሱ የሚያስፈልገው ሆኖ ሳይሆን ለእኛ አርኣያ ይሆነን ዘንድ በዮርዳኖስ ውኃ ተጠመቀ፡፡ በመጠመቁም የዮሐንስ መጥምቅን አገልግሎት አከበረለት፤ መለኮታዊ ክብሩም ተገለጠ።

**«ያንጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ፡፡**

**ዮሐንስ ግን፡- እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል፥ አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን? ብሎ ይከለክለው ነበር፡፡ ኢየሱስም መልሶ፡- አሁንስ ፍቀድልኝ፤ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና አለው፡፡ ያን ጊዜ ፈቀደለት፡፡ ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ፤ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ። እነሆም ድምፅ ከሰማያት መጥቶ፡- በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ።»** *(ማቴ. 3፥13-17)*

በወንጌል እንደነገረን በጥምቀቱ ልጅነታችንን ለመመለስ፥ የአዳምና የልጆቹን የዕዳ ደብዳቤ ለመደምሰስ ሲጠመቅና ከውኃው ሲወጣ፥ እግዚአብሔር አብ ስለ እርሱ ማንነት "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው" በማለት መሰከረ፡፡

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ዓለምን የያዝህ አንተ የሁሉ ፈጣሪ ነህ ሲል በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥ፥ በዮርዳኖስ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ተገለጡ፡፡

አባ ጽጌ ድንግል የእግዚአብሔርን አንድነት-ሦስትነት የገለጡ ጉልህ ክስተቶችን ሲቆጥሩ ዋናዎቹን "በላዕሌኪ ወበዮርዳኖስ ወበታቦር ሥልሰ ጊዜያተ …" በአንቺ ላይ (በእመቤታችን)፥ በዮርዳኖስና በታቦር መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በዚህ መሠረት በዮርዳኖስ ታላቅ ምሥጢር ተገልጧልና በዓለ አስተርእዮ (የመገለጥ በዓል) እንለዋለን።

ጌታችን በዮርዳኖስ በመጠመቅ አስቀድሞ የገለጠልን ሌላኛው ዐቢይ ቁም ነገር የመስቀል ሞቱን ነው፡፡ ለእኛ አርኣያ ሊሆነን በዮርዳኖስ የተጠመቀው እርሱ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጆች እንሆን ዘንድ በጥምቀቱ ወልዶናል፡፡ ይህም ስለ እኛ መተላለፍ በመስቀል ላይ በዋለበት ከጎኑ በፈሰሰው ውኃ ነው፡፡

በርእሳችን ያነሣነው የቅዱስ ያሬድ ቃል የሚያስረዳን እውነትም ይህንን ነው፡፡ "አኮ በወርቅ ኃላፊ ዘተሣየጠነ በደሙ ክቡር ቤዘወነ፥ ወለደነ በጥምቀቱ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን -- በሚጠፋ

ወርቅ/ገንዘብ የገዛን አይደለንም፥ በክቡር ደሙ የዋጀን እንጂ፡፡ በጥምቀቱም ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ወለደን’’ እንዳለ፡፡

የጥምቀታችን ምሥጢር ከሞቱ ጋር መተባበር ነው፡፡ *(ሮሜ 6፥3-5)*

ቅዱስ ቄርሎስ ይህንኑ እውነት “ወበሞተ ዚኣሁ ተጠመቅነ’’ በማለት አገናኝቶታል።

በዚህ መሠረት ጥምቀት በሞተ ወልደ እግዚአብሔር ያገኘነውን መንፈሳዊ ሀብት ሁሉ የምንዘክርበት የልጅነታችን መሠረት ስለሆነ በየዓመቱ እናስበዋለን፡፡

ስለሆነም አምላክ ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ ወረደ፥ ተጠመቀ ብለን አምነን በምንመሰክርበት በዚህ በዓል ላይ ፍቅርና ትሕትናችን የእርሱ ልጆች መሆናችን በሚመሰክርበት መጠን ሊገለጥ ይገባዋል።

በጥምቀት አዲስ ልደትን አግኝተን እንደ ልጅ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስንኖር ለሐዋርያቱ “እርስ በርሳችሁ ብትዋደዱ ደቀ መዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ’’ በማለት የነገራቸው ቃል ይመለከተናል። *(ዮሐ.13፥35)*

በበዓለ ጥምቀት ከተለያየ አቅጣጫ፥ በብዙ ቁጥር የተሰባሰበ ሕዝብ ለታወቀ ዓላማ ይገናኛል፤ የተደረገለትን አስቦ ለማመስገንና በቀጣይ ሕይወቱ የሚያስፈልጉትንም ለመለመን፡፡

ይህ እውን እንዲሆን የሚያስፈልገን ዋና መሠረት ደግሞ ሰላም ነው፡፡

በዓለ ጥምቀት የሰላም፥ የፍቅር፥ የአንድነት፥ የደስታና የመተባበር በዓል ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ቍጥራችን ብዙ ቢሆንም እንኳ የተወለድንባት ጥምቀት አንድ ታደርገናለች፡፡

ከዚህ አንጻር እንደ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ልጆች በፍቅርና በመተሳሰብ ልንመላለስ ይገባል፡፡ የመገለጥ በዓል ነው እንዳልን፥ ይህ ፍቅርና ሰላማችን ለዓለም ሊገለጥ ያስፈልጋል፡፡

የክርስቶስ ልጆች መሆናችንን የሚመሰክር ሌላ እውነት የለምና፡፡

በዓለ ጥምቀት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባለቤትነት ለዘመናት ሲከበር የኖረ ጥንታዊና ትውፊታዊ በዓል ነው፡፡

በመሆኑም በመላዋ ኢትዮጵያ ደረጃ በበዓሉ አከባበር ሥርዓት ውስጥ ተጠብቀው የቆዩ ዕሴቶች አሉ፡፡ እነዚህንም መጠበቅና ለቀጣይ ትውልድ ማስተላለፍ ከበዓሉ ታዳሚዎች ሁሉ የሚጠበቅ ታላቅ ሓላፊነት ነው፡፡

በዓሉ የሁሉም የቤተ ክርስቲያን ልጆች በዓል እንደመሆኑ መጠንም በበዓሉ አከባበር ሂደት ውስጥ ያሉ አካባቢያዊና ባህላዊ መገለጫዎችን ማክበርና በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መሠረት መንፈሳዊነቱን በጠበቀ መንገድ ማስተናገድም ተገቢ ነው፡፡

በበዓሉ ከሚስተዋሉ በርካታ ክንውኖች፡- የቀለማት ኅብር፥ የቋንቋና ባህል ስብጥር አንጻር በርካታ ጎብኚዎች ለታዳሚነት ወይም ለተመልካችነት ወደ ኢትዮጵያ ይመጣሉ፡፡

በተጨማሪም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በዓሉ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፥ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ)

በማይዳሰሱ ቅርሶች ዘርፍ የተመዘገበ ከመሆኑ አንጻር የብዙዎችን ትኩረት እየሳበ ይገኛል፡፡

ይህም የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮና ሥርዐት፥ የሀገርንም በጎ ገጽታ ለዓለም ለማሳየት የሚፈጥረው ዕድል በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡

ስለዚህ በጥምቀት ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን የተወለድን ሁላችን፥ ጌታችን

"መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲከያብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ" *(ማቴ. 5፥16)*

ብሎ እናዳስተማረን፥ ልጅነታችንን የሚገልጽና ቤተ ክርስቲያንን የሚያስከብር በጎ ሥራ ብቻ እንድንሠራ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስም እናሳስባለን፡፡

**በዓሉ የሰላም፥ የፍቅርና የበረከት በዓል ይሁንልን።**

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር**

**አባ ሳዊሮስ**

**የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ፣**
**የደቡብ ምዕራብ ሸዋና የሸገር አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፣የ**
**ምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም**
**የበላይ ሓላፊ**

# የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ
# መልእክት



**ግበሩኬ እንከ ፍሬ ሠናየ  እንግዲህ መልካም ፍሬ አድርጉ**

*(ማቴ ፫፡፰)*

ከሁሉ አስቀድመን አምላካችንና እንኳን ለ፳፻፲፰ ዓ/ም የጌታችን፣ የአምላካችንና የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ጥምቀት ሁላችንንም በሰላም አደረሰን።

ጥንታዊና ቀኖናዊ የሆነው፥ በዓለም ቅርስነት የተመዘገበውን በዓለ ጥምቀት በየዓመቱ በድምቀት የሚከበር መንፈሳዊ የሰላም፣ የአንድነትና የፍቅር በዓል ነው፡፡

አከባበሩም እንደ ማናቸውም ማኅበራዊ ወግና ልማድ ሳይሆን ክርስቲያናዊ ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ ሆኖ የሚያስገኘውን ጸጋና በረከት በማስብ መሆኑን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሁል ጊዜ ታስተምራለች፡፡

ጌታችንም እንደ ሰው ሥርዓት የተጠመቀው እኛን ወደርሱ ለማቅረብ ነው፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ ተጠምቀ በዮርዳኖስ እም ዮሐንስ ከመ ሥርዓተ እጓለእመሕያው እንዘ ያነጽሕ ኵሎ መካነ በመለኮቱ፡ በመለኮቱ ሁሉን የሚቀድስ እንደ ሰው ሥርዓት በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ተጠመቀ'' እንዳለ (ሃ/አበው ዘቄርሎስ ፸) ከበዓሉ ጸጋዎችና የማይጠገቡ ትምህርቶች ውስጥ በነቢዩ ሚልክያስ ''መንገድ አስተካካይ'' *(ሚል.፫፡፩)*

በነቢዩ ኢሳይያስ ''የአዋጅ ነጋሪ ቃል''*(ኢሳ ፵፥፫)* ተብሎ ትንቢት የተነገረለት ቅዱስ ዮሐንስ ''መልካም ፍሬ አፍሩ'' በማለት ያስተማረው ትምህርት ይገኝበታል፡፡

ይኽ በቅዱስ ወንጌል የተነገረ የመጥምቁ አዋጅ ራሳችንንና የእምነት ልባችንን ለበዓሉ ባለቤት ለማዘጋጀት የሚጠቅመን፣ ማንነታችንን ለመመዘን የሚረዳን ቃል ነው።

ቤትን ሳያዘጋጁ እንግዳን መቀበል ደስ እንደማይል ሁሉ፣ ራሱን ያላዘጋጀና ጠማማውን ያላቀና፥ ኅባጣውን ያልገራ፥ ሻካራውን ያላለሰለሰ፥ ኀደሎውን ያልሞላ

“ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር /እነሆ የእግዚአብሔር በግ’’

ብሎ የመሰከረለትን አምላክ በሕይወቱ እንዴት መቀበል ይችላል?

ስለዚህ መልእክቱ አዲስ ልደትን አግኝተን፥ በክርስቶስ ክርስቲያን ተብለን የቀና ሃይማኖታዊ ማንነትና በምግባር የታነጸ ሰብእና እንዲኖረን መሠረታዊ ነው።

መጥምቁም የተላከው የሰውን ልብ እንዲያቀና መንገዱንም አንዲጠርግ ሲሆን የሚቀናውም የእኛ ልብና አእምሮ ወይም ማንነታችን ነው።

“እንግዲህ መልካም ፍሬ አድርጉ’’ (ማቴ ፫፥፰) የሚለው መልእክትና አዋጅ ሦስት ዐበይት ይዘቶች አሉት።

አንደኛው ፍሬ ማፍራትን የሚመክከት ነው፤

ሁለተኛው የምናፈራው ፍሬ መልካም እንዲሆን የሚያስጠነቅቅ ሲሆን

ሦስተኛው መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ በፍሬው ምክንያት ተቆርጦ ያለምንም ጥቅም ወደ እሳት እንደሚጣል ማሳወቁ ነው።

በቅደም ተከተላቸው ስናያቸው እያንዳንዳቸው የእኛን ሕይወት በመግራት ለመንፈስ ቅዱስ ማደሪያና ለዘለዓለማዊ ክብር እንድንበቃ የሚጠቅሙን ናቸው።

በመጀመሪያ በዛፍና በፍሬው የተመሰሉት ሰውና ምግባሩ ናቸው።

የሰው ሕይወት ፍሬ ሊኖረው ይገባል። ፍሬ ማፍራት ዛፍ ራሱን የሚተካበት የረጅም ጊዜ የእድገቱ ወሳኝ ምዕራፍ ነው።

አንድ ተክል ፍሬ ለማፍራት ከችግኝነቱ ጀምሮ ያለው አስተዳደጉ

ወሳኝ ሲሆን ዛፍ የሕይወቱ ዑደት በተገቢው መንገድ ካልተመራ የሚፈለገውን ፍሬ ላያፈራ ይችላል።

ይኸውም ምሳሌ ነው፤ ዛፉ የሰው ሕይወት ሲሆን ፍሬው የሃይ ማኖትና የምግባር መገለጫዎቹ ናቸው።

የሰው ማንነቱ የሚታወቀው በሕይወቱ ፍሬ ነው፥ ጌታችንም በማቴ ፯፡፳ "ከፍሬያቸው ታወቋቸዋላችሁ" በማለት ገልጾታል፤ ፍሬ ያላፈራ ዛፍ ጥቅም የለውም የተረገመም ነው፤ *(ማቴ ፲፩፡፲፪)*

የሰው ልጅ በምድራዊ ሕይወቱ ፍሬያማ መሆን አለበት። የሰው የማንነት መታወቂያ፥ የእምነቱ፥ የጥበቡና ዕውቀቱ፣ የማኅበራዊ ተሳትፎው፣ የግለሰባዊ ምግባሩ፥ የዕለት ከዕለት ተግባሩ የመንፈሳዊና ማኅበራዊ ሕይወት መለኪያዎች ናቸው። ሁለተኛው ስለ መልካም ፍሬ አስፈላጊነት የሚናገር ነው፡፡

በወንጌል እንደተማርነው መልካም ፍሬ የሚያፈራው መልካም ዛፍ ነው፡፡ መልካም ዛፍ ካልሆኑ መልካም ፍሬ ማፍራት ፈጽሞ የማይቻል የማይሞከርም ነው፡፡ መልካም ዛፍ ከሆኑ ደግሞ ክፉ ማፍራት አይቻልም፡፡

ጌታችንም ከእሾህ ወይን ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን? እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል፥ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያደርጋል። መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬ ማፍራት፥ ወይም ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለውም። *ማቴ ፯፥ ፲፮-፲፱)*

መልካም ፍሬ እንዲኖረን እርስ በርሳቸው የማይለየዩ የሃይማኖትና የምግባር ሥራዎች ያስፈልጉናል፡፡ ምግባር ያለ ሃይማኖት ጥቅም የለሽ ሲሆን ሃይማኖት ያለምግባር ሕይወት አልባ ነው፡፡

በአንድ በኩል የቀናች ርትዕት ሃይማኖትን ለጥርጥርና ያለፍርሃት፣ ያለኑፋቄና ያለክህደት፣ በቁሳዊና ዓለማዊ ጥቅም ሳይመሠረት የጠራ ሃይማኖትን ይዞን እስከ መጨረሻው ጸንቶ መገኘት ያለብን ሲሆን በተጨማሪም አምላክን መፍራትና ሰውን መውደድ፥ሀገርና ቤተ ክርስቲያንን ማፍቀር፥ ሃይማኖትን መጠበቅና ማስፋት፣ የእምነት ማንነትን ማክበር፣ ታማኝና ብቁ አገልጋይ መሆን፥ ከኃጢኣት የራቀ ሕይወትን ያለነቀፌታ መኖር፥ አንደበትን ከሐሰት፥ እጅን ከደምና ከስርቆት፥ ሕሊናን ከጣዖትና ባዕድ አምልኮት ማራቅ፤ ቅድስናን በመከተል ድሆችን መርዳት፥ ሕሙማንንና እሥረኞችን መጎብኘት፥ ለተቸገሩት ደራሽ መሆን የሃይማኖት ፍሬ ምንጭ ናቸው፡፡

አባትና እናትን ካለማክበር፥ ሰውን ከመጥላት፣ ራስን ካለመግዛት፣ ከርኩሰትና ከፍቅረ ንዋይ ሕይወትን መጠበቅ መልካም ፍሬ ለማፍራት ወሳኝ ሕግጋት ናቸው። በተለይም ወጣቶች ዘመኑ የደረሰበትን የማኅበራዊ ሚዲያ በአግባቡ በመጠቀም ለመልካም ነገር ማዋል ይኖርባቸዋል፤ ከሱስና አላስፈላጊ ቦታ ከመገኘት በመቆጠብ መልካም ፍሬ የሚያፈራ ማንነትን በመላበስ የነገ መዳረሻን ከማሳመር በላይ በሰውም በፈጣሪም ዘንድ ሞገስ ያስገኛሉ። ሦስተኛው የክፉ ፍሬ ውጤቶች ምሳርና እሳት መሆናቸውን ማወቅ ነው።

ፍሬ ያላፈራች ዛፍ እንደተረገመች፥ እንዲሁ ክፉ ያፈራ ዛፍም በምሳር ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል። መልካም ፍሬ ማፍራት የሁላችንንም ዕጣ ይወስናል፡፡ ውእቱሰ ያጠምቀክሙ በእሳት ወበማይ

- እሽ ብትሉ በመንፈስ ቅዱስ እምቢ ብትሉ በእሳትም ያጠምቃችኋል፤ እንዳለ። *(ማቴ ፫፥፲)*

እሽ ብለን በንሥሓ ቀርበን ለመልካም ፍሬ ብንዘጋጅ መድኀኒታችን በመሠረተልን በማየ ገቦው ባከበርን የሐዲስ ኪዳን ጥምቀት ከብረን ልጅነትን እናገኛለን፡፡

እምቢ ብለን በአመፃችን ብንቀጥል፣ በምሳር ቆርጦ በዘላለማዊ እሳት የማቃጠል ሥልጣን የከሀሊው አምላክ ነው፡፡

ዛሬ በዓለ ጥምቀቱን ስናከበር የምንማረው ይኽንን ነው፡፡

ቅዱስ ዮሐንስ ከመልካም ዛፍ የተገኘ መልካም ፍሬ ነው፤

አባቱ ካህኑ ዘካርያስ፥ እናቱ ቅድስት ኤልሳቤጥ ናቸው፤ ፍሬዋ ገና በማሕፀን ለአምላኩ የሰገደ ነው።

ዛሬ በክህነት የሚያገለግሉ ሥዩማን ካህናትና በጥምቀተ ክርስትና የከበሩ ምእመናን ልጆች ፍሬዎች ናቸው፡፡

መልካም ልጆች እንዲኖሩ መልካም ዛፎች መሆን ግድ ይላል፡፡

በመልካም አስተዳደግ ልጆችን ማሳደግ ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንም ለሀገርም ትልቅ ውለታ ነው።

ዛሬ ሀገርና ትውልድ መልካም ፍሬዎችን ይፈልጋሉ፡፡

ሰላማዊና አስተዋይ፥ በተንኮል ሳይሆን በዕውቀት የተራቀቁ፥ ችግር ፈቺ፥ ሀገርና ወገን አኩሪ፣ ለሥራና ለምርምር የሚተጉ፣ ሃይማኖትን ከምግባር ያዋሐዱ መልካም ልጆችን ማፍራት ትልቅ ኃላፊነት ነው።

በተጨማሪም የብርሃነ ጥምቀቱ ክንውን ሥነ-በዓሉም ሆነ ሥርዓተ ክብሩ በቅዱሳት መጻሕፍትና በሐዋርያት ትውፊት

የሚፈጸም እንጅ ሰው ሠራሽና የፈጠራ ድርሰት ስላልሆነ በዓሉን ስናከበር ሥርዓትና ትውፊትን በመጠበቅ፣ በመከባበርና በፍቅር ሊሆን ይገባዋል፡፡ የተገለጸልንን ድንቅ ምሥጢር እያደነቀን፣ ለተሰጠችን ሰማያዊ ምሥጢር እያመሰገንን፣ ባገኘነው ብርሃናዊ የሃይማኖትና የምግባር ትምህርት ራሳችንን እያነጽን ልናከብረው ይገባናል፡፡ እግዚአብሔር አምላካችን መልካም ፍሬ አፍርተን በጸጋው ከብረን መንግሥቱን ጽድቁን ለመውረስ እንድንችል ያድለን ለሀገራችን ዘላቂ ሰላምና ለቤተ ክርስቲያናችን ጽኑ አንድነትን ይስጥልን።

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር**

**አባ ዲዮስቆሮስ**

**የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊና የራያ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ**
**ጥር ፳፻፲፰ ዓ.ም**

**አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ**

# የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ ሊቀ ጳጳስ

# መልእክት




## “ወናሁ ተርኅወ ሎቱ ሰማይ”

## “እነሆ ሰማይ ተከፈተለት”

በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ "ሰማይ ተከፈተ" የሚለው አገላለጽ አብዛኛውን ጊዜ የእግዚአብሔርን አስተርእዮ (መገለጥ)፣ የእግዚአ ብሔርን መገኘት ፣ አምላካዊ መልእክት ለሰው ልጆች መሰጠቱን የሚያመለክት ነው፤ ይህ ክስተት የተጠቀሰባቸው ዋና ዋና የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚከተሉት ናቸው፤ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር

ወደፊት ሊያደርገው ያለውን ነገር ለነቢዩ ሕዝቅኤል በምርኮ ሳለ የገለጠለት ሰማያትን በመክፈት ነበር (ሕዝ.1÷1) ፤ በሐዲስ ኪዳን ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲጠመቅ ሰማይ ተከፈተለት (ማቴ.3÷16)፤ አይሁድ በድንጋይ ሲወግሩት ሳለ የመጀመሪያው ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ የእግዚአብሔርን ክብር አይቷል፤ "መንፈስ ቅዱስንም ተሞልቶ ወደ ሰማይ ትኩር ብሎ ሲመለከት የእግዚአብሔርን ክብር ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየና፡- እነሆ፥ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ አለ" (የሐዋርያት ሥራ 7÷55-56) ፤ይህም የሚያሳየው በጭንቅ ጊዜ የሚመጣውን፣ ቅዱሳን በመከራቸው ሁሉ የሚጽናኑበትን አምላካዊ መጽናናት ነው፡፡

በራእየ ዮሐንስ መጽሐፍ የሰማይ መከፈት ሁለት ምሥጢራትን ያመለክታል፤ አንደኛው ለቅዱስ ዮሐንስ ሰማያዊ ምሥጥር የተገ ለጠለት መሆኑ ሲሆን (ራእ.4÷1) ፣ሁለተኛው ደግሞ በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጊዜ የሚሆነውን ኀይልና ክብር ያሳያል (ራእ.19÷11)፡፡

**"ሰማይ ተከፈተለት"** የሚለው ቃል የተነገረው ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ በግእዝ "ተረኅወ ሎቱ" በሚለው ንባብ "ሎቱ" የሚለው ቃል አጸፋ ወይም ዝርዝር ይባላል፤ አጸፋነቱም ለክርስቶስ ነው፤ይህም ማለት ክርስቶስን የሚገልጥ ቃል ነው ማለት ነው፤ ምሥጢሩም ሰማይ ለእርሱ መከፈቱ እርሱ ከሰማይ የወረደ ሰማያዊ፣ ተመልሶም ወደ ሰማይ የሚያርግ መሆኑን ያስረዳል፤ "ወአልቦ ዘዐርገ ውስተ ሰማይ ዘእንበለ ዘወረደ እምሰማይ ወልደ ዕጓለ እመሕያው" እንዳለ ወንጌል፤ ትርጉሙም "ወደ ሰማይ የወጣው ከሰማይ የወረደው ክርስቶስ ነው እንጂ ወደ ሰማይ ያረገ ሌላ የለም" ማለት ነው (ዮሐ.3÷13) ፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማየ ዮርዳኖስ፣ በእደ ዮሐንስ ከተጠመቀ በኋላ ከውሃው ሲወጣ ሰማይ ተከፈተለት፤ ቅዱስ ማቴዎስ "ወተጠሚቆ

እግዚእ ኢየሱስ ሶቤሃ ወፅአ እማይ ወናሁ ተርኅወ ሎቱ ሰማይ ወወረደ መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ወነበረ ዲቤሁ’’ ሲል (ማቴ.3÷16) ቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ ደግሞ “ወወፂኦ እማይ ርእየ ተሰጥቀ ሰማይ ወወረደ መንፈስ ቅዱስ ከመ ርግብ ወነበረ ዲቤሁ’’ ይላል (ማር.1÷10) ፤ በሰማይ መከፈትና መዘጋት ኑሮበት አይደለም፤ የተዘጋ ቤት ሲከፈት ውስጡ ያለው ይታያል፤ እንደዚሁም ሰማይ ሲከፈት ምሥጢር ተገልጧልና እንዲህ አለ፡፡

ቀድሞ ለምን ሰማይ ተዘጋ? አሁንስ ለምን ተከፈተ? እንዲዘጋ ያደረገው ምክንያትስ ምን ነበር? መቼም ገነት መንግሥተ ሰማያት በሰው ላይ ዝም ብሎ አልተዘጋም፤ የተዘጋበት ምክንያት ከራቀ/ ከተወገደ መዘጋቱ ይቀራል፤ ሰውና እግዚአብሔርም መገናኘት ይጀምራሉ፤ ቀድሞ የተዘጋው በሰው ኀጢአት ምክንያት ነበር (ዘፍ.324) ፤ መዘጋቱ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ጠብ መኖሩን፣ ለሰው ምሥጢር መከልከሉን ያሳያል፤ አሁን መከፈቱ ደግሞ እርቅና ሰላም መፈጠሩን፣ ምሥጢር መገለጡን ያመለክታል፡፡ “በእንተ ሔዋን ተዐጽወ ኆኅተ ገነት ወበእንተ ማርያም ድንግል ተርኅወ ለነ’’ ትርጉም “በሔዋን ምክንያት የገነት በር ተዘጋ፤ በድንግል ማርያም ምክንያት ተከፈተልን’’ ሲል ቅዱስ ኤፍሬም እንደተናገረው ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን፣ ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ አካላዊ ቃል ሰው ሆኖ ሲጠመቅ ሰማይ ተከፈተ፡፡

ሰማይ ሲከፈት ሁለት ወሳኝ ነገሮች ተከሰቱ፤ አንደኛ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወረደ፤ የመንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል መውረድ ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ከባሕርይ አባቱ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ከባሕርይ ሕይወቱ ጋር በባሕርይ በህልውና አንድ መሆኑን ያስረዳል፤ በዚህም የአንድነት የሦስትነት ምሥጢር ተገለጠ፤ ሁለተኛ አብ ከሰማይ “ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ዘቦቱ ሠምርኩ’’

ማለትም ‘‘በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው’’ የሚል ቃል ተናገረ (ማቴ.3፥17፤ ማር.1፥11፤ሉቃ. 3፥22) ፡፡

በብሉይ ኪዳን ነቢያት በራእይ ካዩት በቀር በዚህ መልኩ በቀጥታ የሰማይ መከፈት ታይቶ የማይታወቅና ከዚህ ቀደም ያልሆነ ዐዲስ ክስተት ነው፤ በሰው ልጆች መካከል ዐዲስና እንግዳ የሆነ ምሥጢር መፈጸሙን ያሳያል፤ ምሥጢሩም አካላዊ ቃል ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን፣ ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ፣ በድንግልና ተፀንሶ በተዋሕዶ አምላክ ወስብእ (ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ) መሆኑ ነው፤ በዚህ ሥራም ሰማያውያንና ምድራውያን አንድ ሆኑ፤ ሰማያውያንን እና ምድራውያንን አንድ ለማድረግም ሰማያዊው ምድራዊ ሆነ፤ ሰማያዊው በምድር በሰዎች መካከል ስለሆነ ሰማይን በመከፈት ማንነቱን፣ ማደሪያውን፣ ክብሩንና ምሥጢሩን ገለጠላቸው፤ አሳያቸው፡፡

የሰማይ መከፈት የጸሎት መድረስ/መሰማት ምልክት ነው፤ በብሉይ ኪዳን ነቢያት ‘‘ሰማዮችን ቀድደህ ምነው ብትወርድ!’’ (ኢሳ.64፥1) እያሉ ይጮኹ ነበር፤ ዛሬ የነቢያት ጩኸት ሁሉ ተሰማ። ተስፋ ደረሰ፤ አምላክ ሥጋን ለበሰ፤ በሰዎች መካከል ተገለጠ፤ የዘለዓለም ሕይወትም ተሰጠ፡፡

በአንድ በኩል የሰማይ መከፈት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል እርቅ መፈጸሙን ያመለክታል፤በሌላ በኩል ደግሞ ሰማይ የሰው ልቡና ነው፤ ሰዎች ልባቸውን ሲከፍቱ የእግዚአብሔርን ድምፅ ይሰማሉ፤ የሰው ልብ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት በኀጢአት ምክንያት ተዘግቶ ነበር፤ አሁን ግን አካላዊ ቃል ሰው በመሆኑና በማየ ዮርዳኖስ ተጠምቆ የእዳ ደብዳቤያችንን በመደምሰሱ ምክንያት እርቅ ተፈጽሟል፤ ለሰው እዳ በደል ካሳ ስለተፈጸመ ሰዎች የእግዚአብሔርን ጸጋ ተቀብለው፣ ኀይለ እግዘኢአብሔርን አግኝተው የሰው ልብም መከፈት ጀምሯል፤ ቃሉን መስማት፣ ማመንና የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ተችሏል፤ ስለዚህ

እግዚአብሔርን የሚፈራና የሚያምን ሰው ልብ እግዚአብሔር የሚመላለስበት ለእግዚአብሔር ማደሪያ የሆነ የተከፈተ ሰማይ ነው፡፡

ከእግዚአብሔር ጋር እርቅ ከተፈጸመ በኑሮም እንዲሁ የተዘጋው ይከፈታል፤ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ ከሁሉም ሰማያውያንና ምድራውያን ጋር ለመስማማት ያስችላል፤ ኑሮአችንን ስናየው ራእይና ተስፋ ተዘግቷል ብለን ተስፋ ቆርጠን ይሆናል፤ “አንኳኩ ይከፈትላችኋል” ያለው ጌታ በጸሎትና በእምነት ደጁን ብናንኳኳ ደጁን ከፍቶ ሊያስገባንና ከእርሱም ጋር ሊያኖረን ዛሬም የታመነ ነው፡፡ የራእይና የተስፋ ሰማይ የሚከፈትልን እንዴት ነው? በእምነት ነው፤ በጥምቀትና በእምነት የተዘጋው ሁሉ ይከፈታል። ስለዚህ በዓሉን ስናከብር የተዘጋውን ለማስከፈት፣ የተበላሸውን ለማስተካከል፣ የወደቀውን ለማንሣት፣ የጠፋውን ለመመለስ እንጠቀምበት፤ በዓል መብላት መጠጣት ብቻ ሆኖ ከቀረ ግን የተከፈተው ሰማይ ደግሞ ይዘጋል፤ ሰማይ ተከፍቶ በረከት አይመጣም፤ሰላም የሚመጣው ሰማይ ሲከፈት ነው፤ የሰማይ መዘጋት የእግዚአብሔርና የሰው መራራቅ፣ የሰላም መጥፋት ምልክት

**በዓለ ጥምቀቱን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰላምና የበረከት በዓል ያድርግልን!**

**ሰላመ እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን!**

**አባ ማርቆስ**

**የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ**
**ሊቀ ጳጳስ**

# የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ
## ዋና ሓላፊ መልእክት



# የብርሃን ልጆች

ብርሃን ሰጭ አካላት ወቅትና ሰዓታቸውን ጠብቀው በሚሰጡት የብርሃን አገልግሎት ለሥነ ፍጥረት ጌጥና ፈርጥ ሆኖ ዓለምን ለማሸብረቅ ብርሃናቸውን ሲለግሱ እናያለን፡፡

ይሁን እንጂ የብርሃን ምንጭ የሆኑ ልዩ ልዩ አካላት የተገኙት ከአንድ እውነተኛ ብርሃን ምንጭ መሆኑ የማያጠራጥር ሐቅ ነው፤ በብርሃን ደካማው ብርቱ ፈሪው ደፋር በመሆን ዕለታዎ ተግባሩን ያከናወናል፡፡

በሚሰጡትም ብርሃን ሌሊትና ቀን ሲፈራረቁ በሚገኘው የጊዜ ገደብ ፍጥረት ሁሉ በእየተፈጥሮ ነገዱ ፍላጐቱን ለማሟላት

ሲወጣ ሲወርድ ማየቱ የሥራና የዕረፍት ጊዜውን የሚወስነው የእነሱን ሥነ ተፈጥሮአዊ መርህ በመከተል ነው ከሚል አስተ ሳሰብና ግምት ላይ ያደርስናል፡፡ ከእንሰሳት ይልቅ የሰው ልጅ አስፈላጊ ተግባሩን ሁሉ የሚፈጽሙት በብርሃን ረዳትነት ነው፡፡

ብርሃን ለሰው ልጆች ብቻ ሳይሆን ለእንሰሳትም ቢሆን ለአጥን ታቸው ጥንካሬን ሰጪ የኃይልና ጽኑእ መሠረታቸው የፀሐይ ብርሃን መሆኑ ይነገርለታል ይልቁንም አረንጓዴ ዕፀዋት ማለትም ከታናሹ ሣር እስከ ታላቁ የሊባኖስ ዝግባ ድረስ አስፈላጊውን ምግባቸውን የሚያዘጋጁት ከፀሐይ በሚያገኙት ብርሃን ተጠቅ መው እንደሆነ የሥነ ፍጥረት ተመራማሪዎች ያስረዳሉ፡፡

እንግዲህ ከብርሃን ዓይነቶች ጥቂቱን ብንመለከት የተለያዩ ብርሃናት በዓለማችን የሚገኙ ከመሆኑም አልፎ ምንጫቸውም እንዲዚሁ የተለያዩ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ከዋና ዋናዎቹ መካከል ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት በቃሉ ኃይል ብቻ የተፈጠሩ በመሆናቸው በሥነ ፍጥረት ሕግ ከመመላለሳቸው በስተቀር የብርሃን ኃይላቸው እንዳይቀንስ ወይንም ብርሃናቸው እንዳይደበዝዝ የሚደረግላቸው መለዋወጫና እንክብካቤ ሳይኖር በጥንተ ተፈጥሮ ጸንተው ሥርዓት ጠብቀው ሲጓዙና ይህን ዓለም በእየክፍለ ጊዜያቸው ሲመግቡ ይታያሉ፡፡

በሌላም በኩል ሰው የፍጥረት ገዥና አዛዥ ስለሆነ በተፈጥሮ የብርሃን ምንጮች ከሆኑት በመነሳት የጊዜ ገደብ ሳያግዳው ተግባሩን ለመፈፀም ያስችለው ዘንድ የተለያዩ የብርሃን መገኛዎችን ፈልስፏል፣ ሰው አዕምሮውን በፈለገው አቅጣጫ ለማስማራት ከመቻሉና ከመራቀቁም በላይ ሙሉ በሙሉ

በሥነ ፍጥረት መጠቀምን እየቻለ ወደ መሄዱ ደረጃ መድረሱ ይበል የሚያሰኝ ግሥጋሴ ነው እንላለን ምን አልባት ወደፊት ካልደረሰበትና ሊያደርገው ካልቻለ በስተቀር የሠራቸውና የፈላስ ፋቸው የብርሃን አስገኝ መሣሪያዎች ሁሉ ሲሰጧቸው የሚሰሩ ሲነሷቸው ደግሞ አገልግሎት የሚያቋርጡ መሣሪያዎች እንጂ በመጀመሪያ ፍልስፍናቸው ያገኙትን የብርሃን አገልግሎት ሳያቋርጡ ሊሰጡ የሚችሉ የብርሃን ምንጮችን እስከ አሁን ሊያስገኝ አልቻለም፡፡

ከዚህም በላይ በተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሹ ዘዴ የተገኙ ብርሃን አስገኝ አካላት ቦታ የሚወስናቸውና ተራራ የሚጋርዳቸው በመሆኑ የብርሃን ምንጭነታቸውን ውስን ያደርገዋል፤ ምንጭነቱም ቀርቶ ጨርሶ የሚጠፋበትም ጊዜ አለ፡፡ እንኳን የሰው ልጅ የተፈላሰ ፈባቸው ቀርቶ ፍጥረት ሁሉ ኃላፊ ጠፊ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት ይህንኑ አስመልክቶ ሲናገር «አቤቱ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው እነርሱ ይጠፋሉ አንተ ግን ትኖራለህ ሁላቸው እንደ ልብስ ያረጃሉ እንደመጐናፀፊያም ትለውጣቸዋለህ ይሰምጡማል አንተ ግን ያው አንተ ነህ» /መዝ.101÷25-28/ በማለት ለዘለዓለም የማይኖሩ መሆናቸውን ሲያስረዳ የብርሃናት አሰገኝ እውነተኛው ብርሃን ግን ምንም ረዳት ኃይል ሳይፈልግ ለዘለዓለም ሲያበራ የሚኖር መሆኑን ሁሉንም አሳልፎ እስከ መቼም መች በብርሃንነቱ ጸንቶ መኖሩን አስቀድሞ ተናግሯል፡፡

ይህንን እውነተኛ ብርሃን ያላወቁ ከማወቅም የዘገዩ ቢኖሩና እውነተኛው ብርሃን ማነው ብለው ቢጠይቁ ግን መልሱ ብርሃናትን ያስገኘ እስከ ወሰን ጊዜያቸውም እንዲያበሩ ያዘዘ ሥርዓት

ምህዋራቸውን ጠብቀው በመዓልትና በሌሊት እንዲመላለሱ ያሰለጠናቸው፤ ሁሉን ማድረግ የሚችል ሁሉ በእርሱ የሆነ መጋቤ ብርሃናት ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ሥግው ቃለ እግዚአብሔር ነው።

ስለ ብርሃን መውጣት ወይም ወደ ዚህዓለም መምጣት ቀደም ብሎ ከሥነ ፍጥረት በኋላም ነቢያት ደጋግመው ሰብከዋል ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ በትንቢቱ «በጨለማ የሄደ ሕዝብ ብርሃን አየ፤ በሞት ጥላ አገርም ለኖሩ ብርሃን ወጣላቸው» በማለት ሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ ተፈርዶበት በእግረ አጋንንት ሲደቀደቅ ለነበረው የሰው ልጅ በሙሉ ልጅነቱን ሊመልስ ብርሃን ክርቶስ ወጣላቸው ነፃነትም ተሰበከላቸው ብሏል፡፡

«ኢየሩሳሌም ሆይ ብርሃንሽ ደርሷልና የእግዚአብሔርም ብርሃን ወጥቶልሻልና ደስ ይበልሽ» በማለት የእውነተኛውን ብርሃን ማንነት ለዓለም የምሥራች ነግሯል /ኢሳ 9፥2-60፥1-3/

በዚህ ብርሃን ተራራ የጋረዳው እመቀ እመቃት የሰወረው፤ ጨለማ የሸፈነው ምንም ምን ሳይቀር ሁሉ ይገለጣል በእሱ ዘንድ የተሰወረ የማይታወቅ፤ የተሸፈነ የማይገለጥ ሊኖር ከቶ አይችልምና ነቢዩ ስለዚህ ሲናገር የረቀቀውንና የተሰወረውን ምሥጢር የሚገልጽ እሱ ነው፤ በጨለማም የሚሰራውን ያውቃል፡፡ በእሱ ዘንድ ብርሃን ነው «ብሏል /ዳን. 2፥22/ ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ» /ዮሐ. 1፥7/ ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛ ብርሃን ወደ ዓለም ይመጣ ነበር በዓለም ነበረ ዓለሙ በእርሱ ሆነ ዓለሙም አላወቀውም» በማለት በብርሃንነቱ አምኖ የብርሃን ልጅ መሆኑን አውቆ ሊመላለስ ባለመቻሉ ከብርሃን ይልቅ ጨለማን እንደ ሚመርጥ የመጣለትን የልጅነት ተስፋ ከመቀበል ከተሰፋ ውጭ ለመሆን ሲሸሽ ይታያል፣ በመሆኑም

ሐዋርያው እንዲህ ሲል ይመክረናል «ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁና አሁን ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ የብርሃኑ ፍሬም በበጎነትና በጽድቅ በእውነትም ሁሉ ነውና ለጌታ ደስ የሚያሰኘውን እየመረመራችሁ እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ ፍሬም ከሌለው ከጨለማ ሥራም ጋር አትተባበሩ’’ /ኤፌ 5፥8/ ብርሃን የሆነው አምላካችን ከጨለማ አበጋዝና ሠራዊቱ ነፃ ሊያመጣን ወዶና ፈቅዶ የዘመኑ ፍፃሜ በደረሰ ጊዜ ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት የተወለደው ድህረ ዓለም ከድንግል ማርያም ያለ አባት ተወልዶ በየጥቂቱ አድጎ በ30 ዘመኑ በዮርዳኖስ ወንዝ በመጠመቅ ልጅነትን አውጆልናል ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀው የዕዳ በደል ደብዳቤያችንን እንደሰውነቱ ረግጦ እንደ አምላክነቱ አቅልጦ ለመደምሰስና ያጣነውን የልጅነት ፀጋና ክብር ለመመለስ ነው።

በመሆኑም እኛ ዛሬ ያለነው አገልጋይም ሆንን ተገልጋዮች በአጠቃላይ በስሙ አምነን በ40 እና በ80 ቀናችን የልጅነትን ፀጋ የተቀበልን አባት የሆነን አምላክ ብርሃን ነውና የብርሃን ልጆች እስከሆንን ድረስ ብርሃናዊ የሆኑ መልካም ተግባራትን ማለትም የብርሃን ሥራ የሆኑትን ፍቅርን እንደ ሸማ ተላብሰን የሰላም አለቃ የሆነውን አምላካችንን በመከተል የሰላም ሰዎችና ሐዋርያ ሆነን ላዘኑትና ለተጨነቁት ፈጥኖ በመድረስ በብርሃኑ ተመላለሱ እንዳለው እንደ ብርሃን ልጆች ልንመላለስ ይገባል ያን ጊዜ የማን ልጆች እንደሆንን ዓለም ሁሉ ያውቀናል፡፡

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር**

**መልአከ ሰላም ዳዊት ያሬድ**

**የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ**

**ዋና ሓላፊ**

# በዓለ ጥምቀት

"ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘያአትት ወያሴስል ኃጢአተ ዓለም፡- እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ።"

*(ዮሐ. 1፡29)*

ጌታችን፣ አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመነ ሥጋዌው ካከናወናቸታላላቅ የትሕትና ተግባራት አንዱ በጥምቀቱ የተገለጠው ነው።

እርሱ መጠመቅ የሚያስፈልገው ሆኖ ሳይሆን የእኛን ጥምቀት ለመባረክና ትሕትናን ሊያስተምረን ወደ ባሕረ ዮርዳኖስ ገሰገሰ፤ ከባሪያው እጅም ተጠመቀ፤ በዚህም ትሕትና ማለት የበላይን ሳይሆን የበታችን ማክበር መሆኑን አስተማረን።

ኃጢአት ወደዚህ ዓለም የገባው በትዕቢት ነበር፤ ጌታችን በትሕትና የጽድቅን መንገድ ከፈተልን።

ትዕቢት ከገነት ጀምሮ የሰው ልጆች የመውደቂያ ገደል ሁኖ ነበር፤ ቃየን ወንድሙ አቤልን በቅናት ተነሣሥቶ ቢገድለውም የሚፈርድ አምላክን መዘንጋቱ ግን ትዕቢት ነበር፤ ጥቅመ ሰናዖር በጅምር የቀረው በትዕቢት ምክንያት ነበር።

የትኛውም ከፍታ ወደ ዝቅታ የሚለወጠው በትዕቢት ሲሆን ታላላቅ ሥልጣኔዎች ዕድሜ የሚኖራቸው በትሕትና ነው፤ ካልሆነ ግን የሰው ልጆች ስጋት ለመሆን ወዲያው ወደ አውዳሚነት ይቀየራሉ።

ሰዎችን ለመርዳት የመጀመሪያው አቅም ትሕትና ነው።

*ትሕትና:- መቆም ፣ ማዳመጥ ፣ ዝቅ ብሎ የሌሎችን ሕመም ማየት ፣ የራስን መውደቂያ በማሰብ ድጋፍ ማድረግ ነው።*



ሙሴ በበረሃ የቀረው ትዕቢት የሚመስል ነገር በመናገሩ ነው።

ራስን ከእግዚአብሔር ጋር ማነጻጸር፣ በጸጋ የተቀበሉትን በድካም እንዳገኙ አድርጎ መቍጠር፣ ‹‹እንዴት ሌሎች ይህን ያጣሉ›› ብሎ መመጻደቅ፣ ተቀብሎ ለመስጠት መሰሰትና የመሳሰሉት በትዕቢት መደብ ላይ ሲገኙ ከሁሉም በላይ አምልኮተ እግዚአብሔርን ማጓደል፣ የፈጣሪን ክብር ለማይገባው መስጠት ደግሞ የትዕቢት አውራ ነው።

ንጉሥ ዖዝያን ሀብተ መንግሥት ተሰጥቶት ሳለ በትዕቢት ምክንያት ‹‹ሀብተ ክህነቱንስ ማን ይከለክለኛል›› በማለቱና

ዕጣን ሊያጥን ወደ መቅደስ በመግባቱ በለምፅ ተቀጣ።

እግዚአብሔር ከብርቱ ንጉሥ ይልቅ ደካማውን ካህን ይወዳል።

ደግሞም ክብራችን ያለው በተሰጠን በመገኘት እንጂ ያልተሰጠንን መፈለግ ትዕቢት ነው።

ክብረ ክህነት በተቃለለበት፣ ካህናት በልጆቻቸው በሚሰደቡበት፣ መስቀልን ቀምቶ አባቶችን ለማባረር በሚመከርበት በዚህ ዘመን የያዝያን ተግሣጽ ትዝ ሊለን ይገባል።

ጌታችን ዮሐንስን መጥተህ አጥምቀኝ ቢል ይቻለዋል፤ ነገር ግን በቀጣይ የሚነሡ ነገሥታት መጥታችሁ አጥምቁን ብለው ካህናትን እንዳያዝዙ መሠረት ጣለልን።

የንጉሥ ልጅ ልዑልና ልዕልትም ወደቤተ ክርስቲያን ሄደው ይጠመቃሉና ጥምቀት የትሕትና ትምህርት ቤት ነው።

ትዕቢት መራራቅ ፣ በርቀት መተኮስ ፣ በግምትና በሐሰት የሰውን ስምና ክብር ማርከስ ነው።

ትሕትና ግን መሄድ ፣ ቀርቦ ማገዝ ፣ ለወንድምም የስሙ ጠባቂ መሆን ነው።

ዓለማችን በልዩ ልዩ ጦርነቶች እየታወከች፤ ኃያላን ሲጋፉም ደካማ አገራት እየደቀቁ እንደሆነ እናውቃለን፤ ሰዎች ከምድር ጨርሰው ጨረቃ ላይ ውድድር ከገቡ አንድ ክፍለ ዘመን ሊያስቆጥር ቢቃረብም የጦር መሣሪያው ሳይንስ በየጊዜው እየረቀቀ ነው፤ ውጤቱ ግን ሰው ራሱን የሚያወድምበት ዘመን መቃረቡን የሚናገር ነው።

ይህች ዓለም በትዕቢት ምክንያት ክፉኛ ተጨንቃ ምጥ እንደ ያዛት ሴት እየጮኸች ሲሆን እግዚአብሔር አምላክ መሪዎችን

አባት ፣ ቤተ ክርስቲያንን እናት አድርጎ ለዚህች ዓለም ሰጥቷልና ለሰዎች ማረፍ ተግተን መሥራት ይጠበቅብናል።

ጌታችን ለመጠመቅ ወደ ዮሐንስ በሄደ ጊዜ ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ የሚጠመቁ ሰዎች ረጅም ሰልፍ ይዘው ስለነበር «**እኔ ጻድቅ ነኝ ልቅደም**» አላለም፤ ደግሞም «**እንዴት በረከሱ መካከል እገኛለሁ**» አላለም፤ ይልቁንም አዲሱ ሊቀ ካህናት ወደ ብሉይ ኪዳኑ ካህን ጋር እስከሚደርስ ወረፋውን በትዕግሥት ጠበቀ ። ከዚህ ታሪክ ዓለም ብዙ መማር ይችላል፤ እውነተኛ ቅድስና ያለው ሰው ሌላው እንዲቀደስለት ባልንጀራ ለማብዛት ይጥራል እንጂ እንደ ርኩስ አይጸየፍም።

ይልቁንም ወገኖቹን ከእሳት ነጥቆ በማውጣት ለርስተ መንግሥተ ሰማያት ያበቃል።

ሰዎችን ለመርዳት በሰዎች መካከል መሆን አስፈላጊ ነው።

ጌታችን ኃጢአታቸውን ተሸክሞ መሥዋዕት የሚሆንላቸውን ኃጢአተኞች በመካከላቸው ሆኖ የልባቸውን ትርታ፣ የእርስ በርስ የፍርሃት ድምፃቸውን ይሰማ ነበር።

ወደ እውነተኛ ንስሐ ብትመጡ በመካከላችሁ እሆናለሁ ሲለን ይህን አደረገ። የታደለው መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስም፡
- በተመለከተው ጊዜ

*“እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ”* በማለት አስተዋወቀው *(ዮሐ. 1፡29)*

ዮሐንስ ስርየትን ያውጅ የነበረው የጥንቱን በግና ፍየል በመሠዋት ሳይሆን እየቀረበ ያለውን የእግዚአብሔር በግ በማሰብ ነበር።

በብሉይ ኪዳን ሰዎች በሚሊየን የሚቆጠሩ በጎችን ቢያቀርቡም መፍትሔ አልተገኘም፤ አንዱ በግ ክርስቶስ ግን ከኃጢአታችን አዳነን። የሰዎች መላ ችግርን ያዳፍን ይሆናል፣ ችግርን የሚያስ ወግደው እግዚአብሔር የሚሰጠን መፍትሔ ነው።

በየትኛውም የአገልግሎት መስክ ላይ ሰዎች እንደ አመጣጣቸው መስተናገድ አለባቸው፤ በዕድሜ የሚበልጡንን የምናከብረው በሰውነት ብቻ ሳይሆን በመኖር ስለሚቀድሙን ጭምር ነው።

የሚያየውን አባቱን ያላከበረ የማያየውን አምላክ አከብራለሁ ቢል ይዋሻልና የሚከተሉት የሚቀድሙትን ካላከበሩ እውነተኛ አምልኮ ሊኖር አይችልም።

መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ የሰዎችን ኃጢአት ሲሰማ እየዋለ ግለሰቦች የከበዳቸውን ሸክም ለእርሱ ያሸክሙት ስለነበር በአገልግሎት ብዛት ደክሟልና ጌታችንን ባየ ጊዜ ማረፍንና በጌታ እጅ የሚጠመቅ የመጨረሻው ተጠማቂ ለመሆን ተመኘ።

ጌታችን ግን ዮርዳኖስ የትሕትና ትምህርት ቤት ስለሆነች ከለከለው። የጌቶች ጌታ ሲሆን በባሪያ እጅ፣ አምላክ ሲሆን በፍጡሩ እጅ ተጠመቀ።

የመስቀሉን መልክ አንድም ቀን ትቶት አያውቅምና በዮርዳኖስ ቅዱስ ዮሐንስ በቀኙ ፣ በደለኞች ተነሣሕያን ደግሞ በግራው ይታያሉ፤ እርሱም በመካከላቸው ሆኖ ወደ ራሱ ይስባቸዋል። በደሉን ላመነ በእግዚአብሔር ዘንድ የበደል እስራት የሚቆረጥበት ምሕረት አለና ትልቁ በደል ንስሐ አለመግባት ነው።

የናዝሬት ነዋሪዎች አምላክነቱን ቢሰውርባቸው አናጢ አድርገው ስለውት ነበር፤ በዮርዳኖስ ግን መሥዋዕት አቅራቢው ሊቀ ካህናት፣

የአለምን ኃጢአት የሚያስወግደው የእግዚአብሔር በግ፣ ተወካፌ መሥዋዕትም እርሱ መሆኑ ተገለጠ ። በናዝሬት በእናቱ ቤት ቢሸሸግ ዕለተ ሞቱ ዘገየ፣ በባሕረ ዮርዳኖስ ግን በዮሐንስ ስብከት፤ እግዚአብሔር አብ ከሰማያት ሆኖ «የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት›› ብሎ ባሰማው ምስክርነት፤ መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል በራሱ ላይ ከታየ በኋላ የቀራንዮ ጉዞው ፈጠነ ። በዚህም በተገለጥን ቀጥር መሥዋዕትነት ቅርብ መሆኑን አስተማረን!

ጥምቀት ጅምሩም ወራጁም የድህ ሀብት ተደርጎ በሚታሰበው ውኃ የሚከናወን ነው። ጥምቀት ትሕትና ነውና ዝቅ ብለው በሚቀዱት ውኃ መከናወን አለበት።

ሁሉም ሊያገኘው በሚችል ውኃ ምሥጢረ ጥምቀት መመሥረቱም ማንም ሰው በሰበብ እንዳይቀር ለማድረግ ነው።

ባለቤቱ በቃልም በተግባርም የቀደሰውንና ያዘዘውን ጥምቀት መናቅ ከድኅነት መጉደልን ያስከትላል።

**ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ታቦተ ምሥዋዕን አክብራ ወደ ባሕረ ጥምቀት የምትወርደው መሠዊያውና መሥዋዕቱ አይለያዩምና የእግዚአብሔር በግ የሆነው ክርስቶስን ለዓለም ለመስበክ ነው።**

ስለሆነም በጉ ኃጢአትን ሊያስወግድ መጥቷልና የጥምቀት በዓላችን ምንም ዓይነት የኃጢአት ነቁጥ የማይታይበት፤ ዘፈንና ሥጋዊ መሻት ሁሉ የሚወገድበት በዓል ሊሆን ይገባል ። ኃጢአተኞች ኃጢአተኛን ይገድላሉ፣ በዚህም እግዚአብሔር እንደ እነርሱ መስሎአቸው አብጀህ የሚል ሽልማትን ከአምላክ በመጠበቅ ይስታሉ፤ ጻድቁ ግን ኃጢአትን ይገድላል፤ ለኃጢአተ ኛውም ይጸልያል፤ በበደል ሽፋኝነትም  አምላኩን ይመስላል ።

ማጠቃለያ፡-

በዓለ ጥምቀት በመላው ዓለም በድምቀት የሚከበር ቢሆንም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ግን ዓበይት ተብለው ከተሰየሙት በዓላተ እግዚእ መካከል በመቶ ሚሊየን የሚቆጠሩ አገልጋዮችና ምእመናን በአደባባይ ወጥተው የሚዘክሩት ታላቅ በዓል ነው። የ2018 ዓ.ም. የጥምቀት በዓልን ስናከብርም ትሕትናን ገንዘብ አድርገን፤ ክህደትን በሃይማኖት፣ ጦርነትን በሰላም፣ መርዶን በብሥራት፣ ኀዘንን በደስታ ለመለወጥ ጠንክረን መሥራት ይጠበቅብናል የሚለው የዘመኑ የቤተ ክርስቲያናችን መልእክት ነው ።

መልአከ ሕይወት አባ ኃይለ ገብርኤል ነጋሽ (ቆሞስ)

የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጸሓፊ

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!!

ጥር ፲፩/11 ቀን ፳፻፲፰/2018 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# ዘመነ መርዓዊ

ዘመነ መርዓዊ እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዘመን (የአውራኅ) አከፋፈል ከታኅሣሥ 28 እና ከብዙኃን እስከ ዘወረደ ዋዜማ ቅዳሴ ያለው ጊዜ ሲሆን በጥቅል አጠራር ዘመነ መርዓዊ በሚል ሥያሜ ይታወቃል፡፡

ይህም ዘመን የቃል ቀዳማዊ ምጽአትና የተስፋው ፍጻሜ የሆነው ልደቱ የሚታሰብበት፣ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ሙሽራ መሆኑን በማሳየት የሚዘመርበት፣ የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ የሆኑት መርዓዊ ወመርዓት (ሙሽራውና ሙሽራይቱ) በዐቂበ ንጽሕና፣ በክብረ ድንግልና ቆይተው ድኅረ ልደት በምስጢረ ቊርባን ጋብቻቸውን የሚፈጽሙበት በዐቢያን አዝማናት መካከል የሚገኝ ንዑስ ዘመን ነው፡፡

በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረው የሰው ልጅ ፍጥረታዊ መንገድን ተከትሎ በፈጸመው የሕግ መተላለፍ ምክንያት ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ ከፈጣሪው ጋር የነበረውን ኅብረት አጥቶ፣ ከዔደን ገነት ምቹ የአትክልት ስፍራ ወጥቶ በእርሱ ምክንያት እሾህንና አሜከላን እንድታበቅል ወደተረገመችው ምድረ ሕማም በመጣሉ ዘመኑ የኃዘን፣ የፍርሃት፣ የመራቆት፣ የቅጣት፣ የምኅላ ዘመን ሆኖ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ተቆጠረ፡፡ *(ዘፍ.3፥22፤ መቅ.ወን.19)*

የተቆጠረው የቅጣቱ ዘመን ሊያልፍ፣ ከገነት በወጣ ጊዜ የተሰጠው ተስፋ ሊፈጸም ጊዜው ሲደርስ ከሦስቱ አካል አንዱ አካላዊ ቃል በስልሳ ሁለተኛው ትውልድ ከተነሣችው፣ ኆኅተ

ገነት ከሆነችው ከቅድስት ድንግል ማርያም በተድላ መለኮት (ለመለኮት በሚገባ ልደት) ተወለደ፡፡

በመወለዱም ሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ ተፈርዶበት ተጎሳቁሎ የነበረው የሰው ልጅ የቀደመ ክብሩ ተመልሶለት፣ ዘመኑ ተለውጦ ብርሃንን ያየበት የሰላም፣ የደስታ፣ የድኅነት የመጽናናት ዘመን በመሆኑ ዘመነ መርዓዊ ተባለ፡፡ *(3.ቀሌ ገጽ 12፤ አክ. ገጽ 98፤ ኢሳ.9፡2፤ የሐ.ሥራ፡20፡፡ መጽ.ምሥጢር)*



ዘመነ ሥጋዌ (አስተ ርእዮተ እግዚእ) በዘመነ መርዓዊ ተጀምሮ በዘመነ መርዓዊ ይፈጸማል ይህም የክርስቶስን ቀዳማይና ዳግማይ ምጽአቱን ያመለክታል፡፡ *(ባህለ ድጓ)*

## የቃለ እግዚአብሔር ወልድ ቀዳማዊ ምጽአትና የተስፋው ፍጻሜ

የቃል ቀዳማዊ ምጽአት እግዚአብሔር ወደ ሰው ልጆች ያደረገው የማዳን ጉዞና ዘመንን ለሁለት የከፈለ የተስፋው ፍጻሜ ነው፡፡

"ይወጽእ መድኅን እምጽዮን ወያአትት ኃጢአተ... ወቦቱ ይረክቡ ተስፋሆሙ አመ አእተትኩ ሎሙ ኃጢአቶሙ - መድኃኒት ከጽዮን ይወጣል ኃጢአትንም ያስወግዳል ኃጢአታቸውን ባራቅሁላቸው ጊዜ በእርሱ ተስፋቸውን ያገኛሉ" ተብሎ አስቀድሞ የተነገረለት ቀዳማዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ የተቆጠረው ሱባኤና የተወሰነው ዘመን ሲፈጸም የጠፋውን ሊፈልግ የተበተነውን ሊሰበስብ ወደእኛ በመምጣቱ ፍጥረተ ሰብእ ጽድቁ ወድቆበት፣ ደስታ ርቆት በነበረው ዘመን ሙሽራው በመወለዱ ዘመኑ ዘመነ መርዓዊ (የሙሽርነት ዘመን) ተብሎ በኍልቈ ዘመን ሊቃውንት ተሰየመ፡፡ *(ኢሳ.59፥20፣ መዝ.13፥10፣ ዮሐ.11፥52፣ ሮሜ.10፥.3)*

በምልዓት በጌትነት ከአብ ከመንፈሰ ቅዱስ ሳይለይ ወደዚህ ዓለም መጥቶ በማይመረመር ግብር የተወለደው መሲሕም ሕዝቡን ከኃጢአት የሚያድን በመሆኑ ስሙ "ኢየሱስ" ተብሎ ተጠራ፡፡

በእርግጥም እርሱ እንደስሙ ትርጓሜ የሁሉ መድኃኒት ሆነ፡፡ *(ኢሳ.6፥3፣ ፥21፣ ሉቃ.2፥21፣ አባ ሕርያቆስ)*

የጸጋ ገዥነቱንና ሰላሙን አጥቶ፣መድኃኒቱ ጠፍቶ የነበረው የሰው ልጅ በምጽአተ ቃል ሰላምን በማግኘቱ የምሥጋና ጊዜ ደርሶ "ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሠምረቱ ለሰብእ-- ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም፣ ሰላም በምድር፣ ለሰው ልጅም በጎ ፈቃድ ሆነ" የሚለው የምሥጋና

ቃል በዘመነ መርዓዊ መጀመሪያ በምድራችን ተሰማ። *(መኃ.2፥12፤ ሉቃ.2፥14)*

ከዘለዓለም ዘመናት በፊት የማይዋሽ መርዓዊ ስቡሕ መድኃኔዓለም ክርስቶስ የሰጠውን ተስፋ ወደዚህ ዓለም መጥቶ በዚህ መልኩ ፈጸመው። *(ቲቶ.1፥2)*

በመኀብኘታችንም ዘመን ከጠላቶቻችን እጅ ድነን ያለፍርሃት በፊቱ በቅድስና እንድናገለግለው ማኅየዊ ቃል በሥጋ ሰብእ ተገልጦ ክብሩን አሳየን *(1ኛ ዮሐ.1፥14)*

ከአርያም ለቤዛነት የመጣው ወደአባቱ ያቀረበን እርሱ "ዘሀሎ ቀዲሙ እምቅድመ አዝማን ወኮነ ይእዜ ሰብአ ወውእቱ ይሄሉ ዘልፈ በመለኮቱ ወበትስብእቱ ዘእንበለ ፍልጠት - ከዘመን አስቀድሞ በቅድምና የነበረ ዛሬ ሰው የሆነ አምላክ ነው። *(ሃይ.አ.ዘጎርጎርዮስ 35፥22)*

እረኛ አጥተው፣ በነፍስ በሥጋ ተጎድተው ለጠፉት ኖላዊ (እረኛ) የሆነው የቤተ ክርስቲያን ሙሽራዋ ክርስቶስ ከላይ በተገለጸው ፍኖተ ድኂን ወደዚህ ዓለም መጥቶ ባሕርየ ሰብእን ባሕርይ አድርጎ (ሥጋን ተዋሕዶ) ድኅነተ ዓለም በመፈጸሙ እርሱ መርዓዊ ስቡሕ ዘለዓለም ተብሎ ዘመኑን ዘመነ መርዓዊ አሰኝቶታል።

## የክብሩ ምሥጋና በዘመነ መርዓዊ

ዘመነ መርዓዊ በወልደ እግዚአብሔር ሰው መሆን ምሕረት ከሌለው ጠላት ድነን ሕይወትን ያገኘንበት፣ ኃጢአት ከእኛ የተወገደበት፣ የደስታ በዓል የምናደርግበት፣ ከአርያም ለኀበኘን መሥዋዕተ ስብሐት የምናቀርብበት፣ ሙሽራውን የመቀበል ዘመን ነው።

ጥዑመ ዜና ወዝክር አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ሙሽራውን በምንቀበልባት ዕለት ኅሪት (በዘመነ መርዓዊ) "ከእኛ ጋር በደስታ በዓልን ያደርጉ ዘንድ አባቶችን እንጥራቸው ከሁሉ በፊት አዳምን እንጥራው እነሆ ከገነት በወጣህ ጊዜ አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፤ ብሎ እግዚአብሔር የተናገረው ተፈጸመ፤ እግዚአብሔር ሥጋን ከሴት ልጅህ ለበሰ የወደድከውን አምላክነት ከሴት ልጅህ በተወለደ በመለኮት ሰው መሆን አገኘኸው፡፡ አስቀድሞ ሰብአ ዝማሬ ሆነህ የተፈጠርከው ዳግመኛ ያከበረህን አመስግነው ታላቅ ነገርን አድርጎልናልና " በማለት ዘመኑ ከኃጢአት ባርነት ነጻ የወጣንበት ለስብሐተ ስሙ የተጠራንበት ዘመን መሆኑን በግልጥ ያስረዳል፡፡

በመሆኑም ዝውእቱ ጊዜ ባርኮት ጊዜ ሰብሐቱ ለመድኃኒነ መፍቀሬ ሰብእ ክርስቶስ - ሰውን የወደደ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የምናመሰግንበት የምስጋና ጊዜ ይህ ነው፡፡

ከዚህም ጋር የሕግ ፍጻሜ ሆኖ ፍርድን የመለሰው ፍሬ ሕይወት ክርስቶስ ጸጋን ከተሞላች ድንግል ተወልዶ ይህንን የምሥራች የሰማንበት ዘመነ መርዓዊ እጅግ የከበረና ከሌሎቹም ጊዜያት የተለየ የደስታ ጊዜ መሆኑን እናስተውላለን *(ሉቃ.1፥26፤ ሮሜ.10፥4)*

መርዓተ ንጉሥ ቤተ ክርስቲያንም የነቢያቱን ቃል መነሻ በማድረግና ሊመጣ ያለው ሙሽራዋ እንዲመጣ አስቀድማ በቃለ ትንቢት "ኅዓ ኃቤየ ወሪደ ኢታጕንዲ - ወደ እኔና ለድኅነተ ዓለም መውረድህ አይዘግይ፤" እያለች ቀዳማዊ ምጽአቱን በመጠባበቅ ለቀበላ መርዓዊ ዝግጅት እንደነበራት ተጽፎአል *(ማቴ.25፥1*

ቅዱስ ያሬድ መዝሙር ዘፀዓተ ክረምት)፡፡ይህም ዝግጅት የክርስቶስን እና የቤተ ክርስቲያንን ፍጹም አንድነት ያሳያል፡፡

**ሙሽራው ክርስቶስ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለው አንድነት (ኅብረት)**

ሙሽሪት ተብላ የምትጠራው፣ለእርሱ ብቻ ሆና የምትኖረው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስትሆን ሙሽራው ደግሞ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡

ይህን ዐውደ ትርጓሜ በሚያጎላው ‘‘ዘቦቱ መርዓት መርዓዊ ውእቱ - ሙሽራ ያለችው ሙሽራ ነው’’ በሚል አገላለጥ ሰማዕተ ብርሃን ቅዱስ ዮሐንስ ባስተማረው መሠረት ቤተ ክርስቲያን ንፁሐ ባሕርይ ለሆነው መርዓዊ ክርስቶስ ታጭታ (ከእርሱ ጋር አንድ ለመሆን) ራሷን አዘጋጅታ በመቅረቧ ሙሽራ ተብላለች (ቆሮ.11፥2)፡፡

በሙሽራውና በሙሽራይቱ መካከልም ያለው አንድነት እጅግ የጸና ነው፡፡ ሙሽራዋ ቤተ ክርስቲያን ባዕድ አምልኮን በማውገዝ ራሷ ለሆነላት ለእርሱ ብቻ በመለየት የሙሽራዋን ፈቃድ ብቻ በመፈጸም ትኖራለች፡፡

‘‘ወትፈቅድ ትትፌሳሕ ምስለ ፍቁራ እምነ ቤተ ክርስቲያን - እናታችን ቤተ ክርስቲያን ከወዳጇ ከክርስቶስ ጋር ደስታን ታደርግ ዘንድ ፈቃዷ ነው፤’’ ሲል ማኅሌታይ ያሬድ እንደገለጸው ከሌላ ጋር ፈቃድ የላትም፥ /ከአመጽና ከጣዖታዊ አምልኮ ጋር አትተባበርም/ ዘለዓለማዊ ደስታዋም እርሱ ብቻ ነው፡፡

እርሱም በዘለዓለም ፍቅር ወዶ ወደ እርሱ ስቦ አቅርቧታልና በሙሽራይቱ ውበት (በምእመን ቅድስና) ደስ ይሰኛል። *(ኤፌ.5፥23)*

በመሆኑም የዓለምን ኃጢአት ያስተሠርይ ዘንድ የመጣው መርዓዊ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን በመውደዱ በውኃ መታጠብ አንጽቶ ወደራሱ አቀረባት አካሉም አደረጋት ቅድስትና ያለነውር ትሆን ዘንድ አከበራት፡፡

አካሉ እንደ መሆኗም በአኗኗሯ ምሥጢራዊት፣ ቅድስትና ንጽሕት እንድትሆን ስለ እርሷ ራሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቷል፡፡ (ኤር.31፥3፣ ኤፌ.5፥16)፡፡ አካለ ክርስቶስ የሆነችው ቤተ ክርስቲያንም ከላይ እንደተገለጸው ለእርሱ በመታመን ሙሽራዋ ክርስቶስ እንደሆነ አውቃ በማመስገንና ከፍ ከፍ በማድረግ እንደምትኖር ‘‘አእመረት ቤተ ክርስቲያን መርአዊሃ- ቤተ ክርስቲያን ሙሽራዋን አውቃለች’’ በማለት ሊቁ ተናግሯል። *(ዝማሬ ገጽ 165)*

ሙሽርነቷን ጠብቃ ራሷን አዘጋጅታ የምትኖረው ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳን ጽድቅ ሥራ የሆነውን የተልባ እግር ልብስ በበጉ ሰርግ እንድትጎናጸፍ ተሰጥቷታል፡፡ *(ራእ.19፥8)*

የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ የሆኑት መርዓዊ ወመርዓት (ሙሽራውና ሙሽራይቱ) ምንጊዜም ቢሆን ሳይለያዩ የክብር አክሊል የቃል ኪዳን ቀለበት እንደሚያደርጉ ሁሉ ክርስቶስም ‘‘አመ ዕለተ መርዓሁ’’ በዕለተ ዐርብ በሚሞሸርበት ጊዜ በራሱ ላይ ያማረ ዘውድ ሳይሆን የሾክ አክሊልን፣ የወርቅ ቀለበት ሳይሆን እሷን የቀደሰበትን የደም ቀለበት ያደረገ ሙሽራ ነው፡፡ *(1ጴጥ.1፥19፣ መኃ.3፥11)*

መርዓዊ ሰማያዊ እየተባለ በሚመሰገነው ክርስቶስ ከብራ፣ በደም ቀለበት ቃል ኪዳን ተጠብቃ ከአምልኮ ጣዖት ርቃ የምትኖረው ቤተ ክርስቲያን ንጽሕት ስለሆነች አፍአዊ ውሳጣዊ ኃጢአት ሳይኖርባት አጊጣ ለዘለዓለም ትኖራለች፡፡

ሥግው ቃል (ሰው የሆነ አምላክ) ለክብሩ ተለይታ የኖረችውን ቤተ ክርስቲያንን (ምዕመንን) ከዚህኛው ዓለም ወደዚያኛው ዓለም ለመውሰድ ዳግመኛ ይመጣል፡፡

በመሆኑም ሙሽራው ዳግመኛ በሚገለጥበት ጊዜ የሰርግ ልብስ ሳይለብስ እንደተገኘው እድምተኛ የሰርግ ልብስ ሳንለብስ (በክርስቶስ የሆነ መልካም ፍሬ) ሳናፈራ እንዳንገኝ ከወዲሁ መዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ *(ማቴ.22÷12)*

ከላይ በስፋት እንዳየነው ከዘመናት በፊት ለክብራችን የተወሰነው ተሰውሮም የነበረው የእግዚአብሔር ጥበብ (ምሥጢረ ሥጋዌ) ጊዜው ሲደርስ በክርስቶስ ሰው መሆን ተገልጦልን "ተወልደ እምዓመቱ ወሰላመ ገብረ በልደቱ" በማለት ከሰማያውያኑ ጋራ በአንድነት ለምስጋና ቆምን *(ሉቃ.2÷13) (ቅ.ያሬድ)*

በክርስቶስ አሰተርእዮ ከተገኘው ፍጹም የሆነ ድኅነት የተነሣ ዓመተ ፍዳ ዓመተ ኲነኔ ይባል የነበረው ዘመን ዓመተ ምሕረት (የምሕረት ዓመት) የሚለውን ስያሜ አገኘ፡፡

በዚህ ምክንያት ዘመነ መርዓዊ ቀዳማዊ ምጽአቱን እና ተዝካረ ልደቱን የምናሰብበት ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ሙሽራ መሆኑን በማሳየት

“ፃዑ ሕዝበ እስራኤል ተቀበሉ **መርዓዌ ሰማያዌ ዘተፈነወ እም ኃበ አቡሁ ርሡይ ወሥርግው ዘመጽአ** /እስራኤል ዘነፍስ ሆይ፥ ከአባቱ የተላከውን ተሸልሞና አጊጦ የመጣውን ሰማያዊ ሙሽራን ለመቀበል ውጡ” እያልን የምንዘምርበት የምሥጋና ዘመን ሆነ፡፡

በአጠቃላይ ዘመነ መርዓዊ **“ወባሕቱ ትመጽእ ሰዓተ መድኃኒት/** የመዳን ቀን ትመጣለች” ተብሎ እንደተጻፈ፤ ወኃቤ ሕይወት ክርስቶስ በሰዓተ መድኃኒት ሁሉንም በራሱ ለማዳን የመጣበት፣ በፍጹም ልባችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ብለን በማመን በስሙ ተጠምቀን ውሉደ ጥምቀት ተብለን የልጅነት ሥልጣን ያገኘንበት የደስታ ዘመን ነው፡፡

በመሆኑም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዚህ የድኅነት ዘመን በዓለ ልደቱን፥ ተዝካረ ጥምቀቱን

**“ክርስቶስ መጽአ ኃቤነ አድኅነነ ወቤዘወነ ወረሰየነ ሕዝበ ዚአሁ”** እያለች በየዓመቱ በደመቀ ሥነ በዓል ታከብረዋለች፡፡ *(ቅ.ኤፍሬም)*


መልአከ ብርሃናት (ቆሞስ) አባ ተክለ ያሬድ ተክለ ጎርጎርዮስ

የቅዱስ ሲኖዶስ ምክትል ዋና ጸሐፊ

## “ወአርአየ ስብሐቲሁ ወአምኑ ቦቱ አርዳኢሁ”
## “ክብሩንም ገለጠ፤ ደቀ መዛሙርቱ በእርሱ አመኑ”

### 1. መግቢያ፡-

የቃና ዘገሊላ ሰርግ ታሪክ ዮሐንስ የጌታን ሞትና ትንሣኤ ለማሳየት ከተጠቀመባቸው ሰባት ምልክቶች አንዱና የመጀመሪያው ነው፡፡

ዮሐንስ በሌሎች ወንጌላት ተአምራት ተብለው የሚጠሩ ልዩ ልዩ የክርስቶስ አስደናቂ ተአምራትን ምልክቶች (Signs) እያለ ይጠራቸዋል። ተአምራቱን ምልክቶች እያለ የሚጠራቸው ደግሞ ተአምራቱ የተፈጸሙት በተአምራቱ ለሚፈጠረው አስደናቂነት ብቻ ሳይሆን ከተአምራቱ ለሚገኘው ትምህርት (ምልክትነት) ተብለው የተፈጸሙና የተጻፉ ስለሆነ ነው፡፡

ተመሳሳይ ዓላማ የነበራቸው ሰባት ምልክቶችም፡-

1) በቃና ዘገሊላ ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ መለወጡ *(ዮሐ.2፥1-11)*
2) በቅፍርናሆም የአንድ የንጉሥ ሹም ልጅን መፈወሱ *(ዮሐ.4፥ 46-54)*
3) ለ38 ዓመታት በሽተኛ የነበረውን ሰው መፈወሱ *(ዮሐ.5፥1-18፣ /4/)*
4) አምስት እንጀራንና ሁለት ዓሣን አበርክቶ 5000 (አምስት ሺ) ሰዎችን መመገቡና 12 መሶብ መትረፉ *(ዮሐ. 6፥1-14)*
5) በባሕር ላይ መሄዱ *(ዮሐ.6፥16-21)*
6) ዘዕውሩ ተወልደን (ከመወለዱ ጀምሮ ዐይነ ስዉር የነበረውን) ዐይን ማብራቱ *(ዮሐ.9፥1-41)* እና
7) አልዓዛርን ከመቃብር ማስነሣቱ ናቸው፡፡

የዚህ ተአምር በዓል ከጌታ የጥምቀት በዓል ተያይዞ በየዓመቱ በጥር 12 ቀን “ቃና ዘገሊላ” እየተባለ ይከበራል፡፡ በእርግጥ

ይህ ቀን ተአምሩ የተፈጸመበት ቀን ባይሆንም የውሃን በዓል ከውሃ በዓል ጋር ለማገናኘት ታስቦ ወደ ጥር ዐሥራ ሁለት እንዲመጣ የተደረገ መሆኑን መምህራን ይናገራሉ፡፡




ነገሩ የውሃን በዓል ከውሃ በዓል ጋር ብቻ ሳይሆን የጌታን በዓል ከጌታ በዓል ጋር ያገናኘ በመሆኑ ጥሩ ሊባል ይችላል፤ *ጥምቀትም፣ የቃና ዘገሊላ ተአምርም በጌታ የተፈጸሙ ናቸውና፡፡*

የዚህ ክፍለ ንባብ ታሪክ ዋና ዓላማ በቁጥር 11 የሰፈረው ነጥብ ነው፡፡

"ኢየሱስ ይህን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ፤ ክብሩንም ገለጠ፤ ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ" ይላል፡፡ ይህ ጥቅስ ሦስት ነጥቦችን ይነግረናል፤ አንደኛው በገሊላ ቃና በሰርግ ቤት የተደረገው ተአምር

የመጀመሪያው ምልክት ነው፡፡ ሁለተኛ በዚህ ምልክት ኢየሱስ ክርስቶስ ክብሩን ገልጧል፤ ሦስተኛው ደግሞ ደቀ መዛሙርቱ በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ የሚል ነው፡፡

ዮሐንስ የወንጌሉን ታሪክ ሲጽፍልን የተነሣበት ዓላማ "ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ፣ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፏል" *(ዮሐ.20÷31)* የሚለው ነው፤ ይህ ተአምር የተጻፈበት ዓላማም ወንጌሉ ከተጻፈበት ዓላማ ጋር አንድ ነው፡፡

## 2. በሦስተኛው ቀን ማለት ምን ማለት ነው?

ሦስተኛው ቀን ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ፊልጶስንና ትናኤልን ከጠራበት አንድ ቀን በኋላ በሦስተኛው ቀን ማለት ነው፤ በምዕራፍ 1 ቁጥር 29፣ 35 እና 44 ሦስት ቦታዎች ላይ "በነገው" የሚል ቃል ስላለ ከዚህ ተነሥተን 2÷1 "በሦስተኛውም ቀን" ያለው ንባብ በቁጥር 44 "ወበሳኒታ ፈቀደ ይሑር ገሊላ" ማለትም "በነገው ኢየሱስ ወደ ገሊላ ሊወጣ ወደደ" ከሚለው ንባብ ጋር የተያያዘ መሆኑን መረዳት እንችላለን፡፡ ፊልጶስንና ናትናኤልን ከጠራበት ቀን ጀምሮ "በሦስተኛው ቀን" በገሊላ ቃና በሰርግ ቤት ኢየሱስ ክርስቶስ ተገኘ፡፡

## 3. የገሊላ ቃና የት የምትገኝ ቦታ ናት?

ይህች ቃና ጌታ ካደገባት ከናዝሬት ሰባት ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ የምትገኝ መንደር ናት፤

"ቃና ዘገሊላ" የሚለው ቃል ሌላ ቃና የምትባል ቦታ ያለች መሆኑን ያስረዳል፤

ኢየሱስ ክርስቶስ ከጥቂት ቀናት በፊት ከዮርዳኖስ ማዶ

ቢታንያ ውስጥ "ቤተ ራባ" በተባለ ቦታ እንደነበረ በ1፥28 ስለተገለጠ አሁን ከቤተ ራባ ወደ ቃና ዘገሊላ መምጣቱን እንረዳለን፡፡

ከቤተ ራባ ወደ ቃና ለመምጣት ከ2 እስከ 3 ቀናት ሊወስድ እንደሚችል ይገመታል፡፡

ቃና የናትናኤል ሀገርና የቅፍርናሆም ሹም ልጅን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃሉ የፈወሰበት ቦታ ነው *ዮሐ. 21፥2፤4፥46-54)*

ቃናን የጠቀሰና የምትገኝበትን ቦታ በተመለከተ መረጃ የሰጠን ዮሐንስ ብቻ ነው፡፡

በሌሎች ወንጌላት ቃና አልተጠቀሰችም፡፡ ኢየሱስና እናቱ፣ ለሰርግ መገኘታቸውና በዚያም ዘመዶች የነበሯቸው መሆኑ ቃና ከናዝሬት ብዙ የራቀች እንዳልነበረች ሊጠቁመን ይችላል፡፡

በቅሪተ አካላት ጥናት (አርኬኦሎጂ) ቃና የት አካባቢ ትገኝ እንደነበረ የሚጠቁሙ የተወሰኑ ማስረጃዎች ተገኝተዋል፡፡

## 4. ጌታ ወደ ሰርጉ ቤት መጠራቱና መገኘቱ

***ኢየሱስ ክርስቶስን*** ወደ ሰርጉ ጋበዙት ፤ እርሱም የራሱን ክብር ሳይሆን የእኛን ጥቅም ይመለከታልና መጣ፤ *"የባሪያን መልክ" (ፊል.2፥7)* መያዝን እንደማይረባ ነገር ያልቆጠረው እርሱ በባሪያዎቹ ሰርግ መገኘትን አልናቀም፤ *"ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር" (ማቴ. 9፥11)* የተቀመጠው እርሱ በሰርግ ቤት ከታደሙት ጋር መቀመጥን እምቢ አላለም።

## 5. የድንግል ማርም ጥያቄ

የድንግል ማርያም ጥያቄ በወንጌል እንደተጻፈው "የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም" የሚል ነው፤

ይህን እንዴት ማወቅ ቻለች? ለሚለው ጥያቄ ዘመድ ስለነበረችና በቅርበት እያገለገለችና እየተቆጣጠረች ስለነበረ ሊሆን ይችላል፤

ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ሲታደሙ (ሲጠሩ) እርሷ ቀደም ብላ በቤተ-ሰብነት የተገኘች መሆኑን ወንጌሉ ያስረዳል፤ ሌሎች አገልጋዮች ማለቁን ዐውቀው ነግረዋት ሊሆንም ይችላል፤ የጌታን መልስ ከሰማች በኋላ ለአገልጋዮቹ የሚላቸሁን ሁሉ አድርጉ ብላ አዘዘቻቸው፡፡ እርሷ ልጇን መጠየቅዋ ግን አስቀድሞ በቅዱስ ገብርኤል ብሥራት ከተነገራት ጊዜ ጀምሮ የእርሱን ማንነት ለማወቅና ተአምራቱን ለማየት ችላ ስለነበረ እርሱ አንድ ተአምር በማድረግ ችግሩን ይፈታል ብላ አምና ነው፤ ይህንም ከታሪኩ አንጻር ተረድቶ እምነቷን ማየት አያስቸግርም፡፡

## 6. የኢየሱስ ክርስቶስ መልስ

በ2÷4 እንደተጻፈው ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም ለቀረበለት ጥያቄ የሰጠውን መልስ እናነባለን፡፡ ቃሉም "አንቺ ሴት ከአንቺ ጋር ምን አለኝ? ጊዜየ ገና አልደረሰም አላት" የሚል ነው፡፡ ይህ ጥቅስ ሦስት ነጥቦችን ይዟል፡፡ እነዚህም፡-

(1) አንቺ ሴት (2) ከአንቺ ጋር ምን አለኝ? (3) ጊዜየ ገና አልደረሰም የሚሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ነጥቦች ምን ማለት እንደሆኑና በታሪኩ እንዲሁም በዮሐንስ ወንጌል ዐውድ ምን ማለት እንደሆኑ ከዚህ አልፈንም በቤተ ክርስቲን አባቶች ትምህርት ምን ትርጉም እንደተሰጣቸው እንመልከት፡፡

<u>አንቺ ሴት</u>፡-

፡- ይህ ቃል ለዘመናችን አንባብያን የሚያውክ እንግዳ አገላለጽ ይመስላል፤

ነገር ግን በጥንት የእስራኤል ባህል መሠረት ሲታይ ይህ ቃል የንቀት ሳይሆን የማክበርና የርኅሩኅነት አነጋገር ነበር፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለም እናቱን የጠራት "አንቺ ሴት"

በሚለው አገላለጥ ነበር(ዮሐ.19÷26) ሆኖም ኢየሱስ በዚህ ቦታ "እናቴ" አለማለቱ የእናትነት ክብሯን ንቆ አይደለም፤

"አንቺ ሴት" የሚለው አነጋገር የማቃለል ቢሆን ኢየሱስ ክርስቶስ እናቱን ያውም በመስቀል ላይ ሳለ ጭምር አንቺ ሴት ብሎ ሊጠራት አይችልም ።

## ከአንቺ ጋር ምን አለኝ?

በግእዝ "ምንት ብየ ምስሌኪ" የሚለውን ቃል የአንድምታ ትርጓሜ መምህራን ሲተረጉሙ ሦስት አማራጭ ትርጉሞችን አቅርበዋል፤

አንደኛው፡- "ካንቺ ጋር ምን አለኝ? ማለት ውሃውን ጠጅ አድርግላቸው ብትይኝ አይሆንም እልሽ ዘንድ ከአንቺ ጋር ምን ጠብ አለኝ? አላት" ይላል።

ሁለተኛው፡- *"አንድምታ)* ውሃውን ጠጅ አድርግላቸው ብትይኝ አይሆንም እልሽ ዘንድ ውሃውን ጠጅ ላላደርግ ከሰርግ ቤት ተጠርቼ መጥቻለሁን?፤ ውሃውን ጠጅ ላላደርግላቸው ነውን? አላት" የሚል ሲሆን

ሦስተኛው፡- "*አንድምታ)* በአምላክነቱ አገብሮ፣ ተአዝዞ (ግዴታ፣ መታዘዝ) እንደሌለበት ለማጠየቅ ነው።

## "ጊዜየ ገና አልደረሰም"፡-

"ጊዜየ ገና አልደረሰም" የሚለው ዐረፍተ ነገር ጌታ ከሚሞት ትበትና ከሚነሣበት ጊዜ ጋር የተገናኘ ቃል ነው፤ ይህን ቃል ዮሐንስ ወንጌላዊ እዚህ ቦታ ብቻ የተጠቀመው አይደለም፤ ዮሐንስ በወንጌሉ ውስጥ በብዙ ቦታ ተናግሮታል፤ ለምሳሌ፡-

"ጊዜየ ገና አልደረሰም" *2÷4 እና 7÷ 6*

"ጊዜው ገና ስላለደረሰ" 7÷30

"ጊዜው ገና አልደረሰምና" *8÷20*

"ሰአቱ ደርሷል" *12÷23*

"ሰአቱ እንደደረሰ አውቆ" *13÷1*

"ሰአቱ ደርሷል" *17÷1*

የሚሉትን ጥቅሶች ተከትለን ስናጠናው ሰአት ወይም ጊዜ የሚለው ቃል ከኢየሱስ ክርስቶስ የሞት ጊዜ ጋር የተያያዘ ነገር እንደሆነ እንረዳለን፡፡

ከምዕራፍ 12 ጀምሮ ቀደም ሲል ጊዜ እየተባለ ይጠራ የነበረው ሰአት ወደ ሚል የአጭር ጊዜ መጠሪያ መቀየሩ ጌታ ሞቱ እንደቀረበ በግልጥ ይናገር እንደነበረ ያሳያል፡፡

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ጌታ ጊዜየ ገና አልደረሰም ሲል እንደ ፍጡር በጊዜ የተወሰነና በፈለገው ጊዜ ተአምራት ማድረግ የማይችል አይደለም፡፡ ሁሉንም በራሳቸው ጊዜ በሥርዐት (order) የሚሠራ አምላክ ስለሆነ ነው እንጂ ብሏል፡፡

ለምሳሌ፡- ልደቱን፣ሞቱን፣ ዕርገቱን፣ ዳግም ምጽአቱን ሁሉ በአንድ ቀን ማድረግ ይችል ነበር፡፡ ነገር ግን ሁሉንም በሥርዓት በየጊዜያቸው አደረጋቸው ይላል፡፡ "ጊዜየ ገና አልደረሰም" ካለ በኋላ ለምን ተአምር አደረገ? ለሚለው ጥያቄ ደግሞ ዮሐንስ አፈወርቅ ሁለት ምክንያቶችን ይሰጣል፡፡

1) ጊዜየ ገና አልደረሰም እንዳለ ሁሉ እርሱ ያን ጊዜ ተአምር ባያደርግ ኖሮ እንደ ማንኛውም ፍጡር በጊዜ ገደብ (በጊዜ ውሱንነት) ውስጥ ያለና የጊዜ ተገዥ አድርገው ላሰቡት ሰዎች ማስረጃ በሆነ ነበርና እርሱ በጊዜ የተወሰነ እንዳልሆነ ለማጠየቅ ተአምር አደረገ፡፡

2) የእናቱን ጥያቄ አልተቀበለም ብለው እናቱን የማያከብር፣ እናቱ የፈለገችውን ነገር ማድረግ የማይፈልግ አድርገው ባሰቡት ነበርና ጥያቄዋን እንደተቀበለ ለማጠየቅ ነው፡፡

## 7. የማንጻት ልማድ የሚፈጸምባቸው የድንጋይ ጋኖች ምንድን ነበሩ?

ጌታ ውሃውን ወደ ወይን የቀየረው ወይን የነበረባቸውን ጋኖች ተጠቅሞ አይደለም፤

የመንጻት ሥርዐት የሚፍጸምባቸውን ጋኖች ተጠቅሞ ውሃውን ወደ ወይን ለወጠ፤

የወይን ጠጅ የነበረባቸው ጋኖች የመብል የመጠጥ ሥርዐት የሚፈጸምባቸው ጋኖች ናቸው፤

የመንጻት ሥርዐት ግን ሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ዓላማ ያለው ሥርዐት ነው፤

ስለዚህ ጌታ ከመብላትና ከመጠጣት ሥርዐት ወደ መንፈሳዊ ነገር አልፎ ተአምር አደረገ፡፡

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ይህን ሲያብራራ እንዲህ ይላል፤

"ወንጌላዊው *አይሁድም እንደሚያደርጉት የማንጻት ልማድ* በማለት የተናገረው ያለምክንያት አይደለም፤ ከተጠራጣሪዎች አንዱ የወይን ጋን ውስጥ ጥቂት ቀርቷል ብሎ እንዳይጠረጥር፣ ውሃም በዚያው ወይን በነበረበት ጋን ላይ ተቀድቶ ተደባልቆ ነበረ፤ የማይጠፍጥ ወይንም ተሠራ እንዳይል ነው ይህን ያደረገው፤ ስለዚህ ጋኖቹ በጭራሽ የወይን መያዣ እንዳይደሉ ለማሳየት

*"አይሁድም እንደሚያደርጉት የማንጻት ልማድ"* አለ ።

ምክንያቱም ፍልስጤም ጥቂት ውሃ ብቻ የሚገኝባት ሃገር

ናት ፣ ጅረትና ፏፏቴም በየቦታው አይገኝባትምና እነርሱ ሁል ጊዜ የውሃ ጋኖችን በውሃ ይሞሉ ነበር፤ በዚህም ጋኖቹ በማንኛውም ሰአት በውሃ የተሞሉ ከሆነ እጅን ለማንጻት የሚሆን ውሃ ፍለጋ ሁል ጊዜ ወደ ወንዝ እንዳይወርዱ ነው።

በመቀጠልም ''ምልክቱን/ተአምራቱን ጋኖቹ ላይ ውሃ ከመሙላታቸው በፊት ያላደረገው ስለምንድን ነው? ይህ እስካሁን ከተደረጉት ተአምራት የሚደንቅ አይሆንም ነበርን?'' በማለ ይጠይቅና እንዲህ በማለት ይመልሳል፤ ''የሆነን ነገር ወደሌላ መቀየር አንድ ነገር ነው፤ ከምንም መፍጠር ደግሞ ሌላ ነገር ነውና፡፡ በእርግጥም ኋለኛው እጅግ የሚደንቅ በሆነ ነበር፤ ነገር ግን ለብዙኃኑ የሚታመን ባልሆነ ነበር። በዚህም ምክንያት ሆን ብሎ በቀላሉ ተቀባይነት ያገኝ ዘንድ የምልክቱን/የተአምራቱን ታላቅነት አነስ ያደረገዋል'' ይላል፡፡ ሌላ ጥያቄም ''ነገር ግን አንድ ሰው እንዲህ ሊል ይችላል'' በማለት ይጠይቃል፤ ''ወደ ወይን የቀየረውን ውሃ አገልጋዮቹ እንዲያመጡት ከማድረግ ለምንድን ነው ራሱ ያላመጣው? ይህን ያደረገው ከላይ ባልነው ተመሳሳይ ምክንያት ነው፤

ውሃውን ያመጡት ሰዎች ማንም ሰው ደፍሮ የሆነው ነገር ምትሐት ነው እንዳይል አገልጋዮቹ ጋኖቹን በውሃ የሞላናቸው እኛ ነን ብለው ይመሰክሩ ዘንድ ነው'' ይላል፡፡

## 8. መልካሙን የወይን ጠጅ፣

''አሁን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው ስጡት አላቸው፤ ሰጡትም። አሳዳሪውም የወይን ጠጅ የሆነውን ውሃ በቀመሰ ጊዜ ከወዴት እንደ መጣ አላወቀም፤ ውኃውን የቀዱት አገልጋዮች ግን ያውቁ ነበር፤ አሳዳሪው ሙሽራውን ጠርቶ ሰው ሁሉ አስቀድሞ መልካሙን

የወይን ጠጅ ያቀርባል፥ ከሰከሩም በኋላ መናኛውን፤ አንተስ መልካ ሙን የወይን ጠጅ እስከ አሁን አቆይተሃል አለው'' *(ዮሐ 2፥8-10)*

አሳዳሪው ጌታ የለወጠውን የወይን ጠጅ ከቀመሰ በኋላ የቀደመውን መናኛ ፣ ያሁኑን መልካም (ማለፊያ) ሲል የገለጠው በትክክል ነበር፤ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ እንዲህ ይላል፤

''አሁን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው ስጡት'' ብሎ ያዘዘ ጌታ ነው፤ የቀመሱት ሁሉም ታዳሚዎች አይደሉም፤ ''የሰከሩ ሰዎች ነበሩ፤ የአሳላፊዎቹም የመቅመስ ብቃት በስካር ተበላሽቶ ነበር፤ የተሠራውን ነገርም መቅመስ አይችሉም ነበር ወይም ስለ ሆነው ነገር መወሰን አይችሉም ነበር፤

ስለዚህ እነርሱ ስለሰከሩ የተለወጠው ነገር ወሃ ይሁን ወይን አያውቁም ነበር'' እንዳይሉ ይህን አደረገ፤

አሳላፊው ራሱ በተናገረው ነገር ይህን አሳይቷል፤

ምክንያቱም ይህን ጥርጣሬ ወንጌላዊው ዮሐንስ በወንጌሉ አስወግዷል።

ወንጌላዊው ''ታዳሚዎቹ አስተያየታቸውን ሰጡ'' አላለም፤ ነገር ግን እስካሁን ያልሰከረው፣ አንዳች ነገርም ያልቀመሰው አሳዳሪው አለ እንጂ። እንዲህ ያለ ግብዣ ላይ አሳዳሪ የሚሆኑ ሰዎች ራሳቸውን የሚቈጣጠሩ እንደሆኑ ይታወቃልና፡፡ እነሱም ማሳለፉን እንደ አንድ ኃላፊነት ይዘው ሁሉንም ነገሮች በሥርዐትና በትክክል እንዲከናወኑ የሚያደርጉ ሰዎች ናቸው።

ስለዚህ ጌታ ስለተደረገው ነገር እንዲመሰክር እንዲህ ያለን ከስካር የራቀን ሰውን ጠራ።

*''ለአሳዳሪው ቀድታችሁ ስጡት'' አለ* እንጂ ''ለተቀመጡት (እድምተኞች) ቅዱላቸው'' አላለምና ።

## 9. የተአምሩ ዋና ዓላማ (ማጠቃለያ)

*"ክብሩንም ገለጠ ፤ ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ"*

ክብሩ ምንድነው? ክብሩ ተአምሩ ነው፤

የገለጠው ክብሩ ተአምሩ ነው፤ ተአምሩን አደረገ፤ ክብሩ ጌትነቱ ነው፤ ጌትነቱን ገለጠ፤

ክብሩ የተገለጠው ለማነው? ተአምሩን የሚያውቁ ጌታ፣ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምና አገልጋዮቹ ነበሩ፤ አሳዳሪው፣ ሙሽራውና ታዳሚዎቹ ምንም የሚያውቁት ነገር አልነበረም፤

አሳዳሪውን "ወኢያእመረ እምኀበ አምጽእዎ" ይለዋል፤ "ከየት እንዳመጡና እንደሰጡት አላወቀም" ማለት ነው፤ ቀምሶ ማድነቅና መልካም ወይን መሆኑን መመስከር እንጂ እንዴትና በምን መንገድ እንደተገኘ አላወቀም፤ ይህ ከሆነ እንዴት "ክብሩን ገለጠ? ለማን ክብሩን ገለጠ?

ወንጌላዊው "ክብሩን ገለጠ" ካለ በኋላ በመቀጠል እንዲህ ይላል፤

*"ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ"፡፡* ክብሩን የገለጠው ለሚያምኑ ነው፤

ያመኑ ደግሞ ደቀ መዛሙርቱ ናቸው፤ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አስቀድሞም የልጇን ማንነት ታውቃለች፤ ታምናለችም፤ ለደቀ መዛሙረቱ ግን ገና ክብሩና ማንነቱ እየተገለጠላቸው ነበርና ክብሩንና ተአምራቱን ዐይተው አመኑ፤ የተአምሩ ዋና ዓላማም ይህ ነበርና አሳዳሪው ከቀመሰና ካደነቀ፣ ደቀ መዛሙርት ተአምሩን ዐይተው ካመኑ በኋላ ታዳሚዎቹ ወይን በመጠጣት መቀጠል አለመቀጠላቸውን ምንም ሳይል ታሪኩ በዚህ አበቃ፤ የጌታን ክብር ከማየት የበለጠ ምን አለ?

ክብሩን ዐይቶ ከማመንስ የበለጠ ምን አለ ? ይህን ዜና ከመናገር በላይ የሆነ የቀረ ምን ጉዳይ አለ?

የዚህ ተአምር ቁልፍ መልእክት ተደርጎ ሊታይ የሚገባው ሌላ ነጥብ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እናትነትና ርኅራኄ የተገለጠበት ተአምር መሆኑ ነው፤ "ወይንኮ የላቸውም" ያለችበት የርኅራኄ ቃል በልጇ በወዳጇ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ተሰማ፤ ተሰምቶ ብቻ አልቀረም ፤ ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ በመለወጥ በተግባር ልመናዋን ፈጸመላት።

ሌላው የመጨረሻ ነጥብ ይህ ተአምር በሰርግ ቤት መደረጉ የከበረ መልእክት አለው፤ ጋብቻ ከሥነ ፍጥረት ጀምሮ የከበረ ነው፤ ኀጢአት የሰውን ሁለንተና ስላበላሸ የጋብቻ ክብርም በኀጢአት ምክንያት ተበላሽቶ ነበር። አሁን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምና ደቀ መዛሙርት በመገኘታቸው የጋብቻ ክብር ተመለሰ፤ ዛሬ ትዳርን ክርስቶስ በተገኘበት መጀመር በረከት ነው፤ ዘላቂነቱም ይጸናልና ምእመናን ትዳር ሲመሠርቱ የእግዚአብሔርን ፈቃድና ዓላማ በጋብቻቸውም በረድኤት የተገኘ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

የቃና ዘገሊላ በዓልን ስናከብር ክብሩና ማየትና በእርሱ ማመናችንን በመጽናት፣ ሌሎችንም ወደ ክብሩ በመጥራት እንድናከብር በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስም በማሳሰብ፣ በዓሉ የበረከትና የአንድነት፣ የክርስቶስን ክብር የምናይበትና የምናሳይበት ይሆንልን ዘንድ አምላካችን ይርዳን!

መጋቤ ብሉይ አእመረ አሸብር ዓለማየሁ
በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት
የትምህርትና ማሠልጠኛ መምሪያ ዋና ጸሓፊ

## ይእቲኬ መድኃኒት እንተ ኀሠሥዋ ወየድዋ ነቢያት

## ነቢያት ተግተው የፈለጓት እና የመረመሯት መድኃኒት ይች ናት

*(1ኛ ጴጥ. ምዕ. 1-10)*

ይህ በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ወንጌል ድቃላ ሕግ ናት፡፡

አባታችን አብርሃም ሕጋችን ኦሪት ጸሐፊያችን ሙሴ ብለው ለሚያምኑ ዕብራውያን የተሰበከ የቅዱስ ጴጥሮስ ትምህርት ነው፡፡

የትምህርቱ ዓላማ የወልድን በለቢሰ ሥጋ መገለጥ እና መወለድን አስረግጦ ማስረዳት ነው።

ቅዱሳን ነቢያት በዘመን ሂደት ያለዕረፍት በጾም በጸሎት የደከሙለት ትንቢት የተናገሩለት ሰው መሆኑን መድኃኒት ብሏታል።

ነቢያት በትንቢት ሐዋርያት በስብከት ለገሐዱ ዓለም የመሠከሩትን ልደተ እግዚእን ሊቃውንቱም እንደሚከተለው በምሥጢር ተባብረውበታል።

**ነአምን ልደቶ ዘኢኮነ እምሰብእ ወኮነ ከመ ሰብእ**

/በሰው ዘር ያልሆነ ግን እንደ ሰው የሆነውን ልደቱን እናምናለን/

ልደተ እግዚእ ለሰው ልጅ ፍጹም ሥርየትና ዕርቅ ግልጥ ሆኖ የታየበት ዕለት ነው።

በጌታችን መድኃኒታችን መወለድ መስተጻርራን የነበሩ ሰማይና ምድር፣ ሰውና መላእክት በአንድነት ለምስጋና ታድመዋል።

የእረኞች አንደበት ከመላእክት ጋር ለሰማያዊ ምስጋና ኅብረት አድርጓል፡፡

ግዕዛን የሌላቸው እንስሳት ሠሪያችን መጋቢያችን፣ በዘባነ ኪሩቤል በሰማያት የምትገለጥ አንተ ነህ ሲሉ እስትንፋሳቸውን ገብረውለታል፡፡ ነገሥታተ ምድር በሥልጣንህ ሽረት በመንግሥህ ህልፈት የሌለብህ ንጉሠ ነገሥት አንተ ነህ ሲሉ ወርቅን ለመንግሥቱ፣ ዕጣንን ለክህነቱ፣ ከርቤን ለሕማሙ እጅ መንሻን አብርክተውለታል፡፡



ልደተ እግዚእ ትንቢተ ነቢያት እውን የሆነበት ሐሳበ አይሁድ ውድቅ የሆነበት ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም ከጻድቁ ዮሴፍ ጋር ያን ልዩ ክብር የዩበት/ግብረ መንፈስ ቅዱስ/ ሰማይና ምድር የተገናኙበት ዘመነ ምሕረት የጀመረበት ረቂቅና ልዩ ልደት ነው።

ሊቁ ሲገልጠው "ተወልደ ለነ መድኅን አምጣን አኮ ዘተወልደ ዘኢሀሎ አላ ዘሀሎ ዘእምቅድመ ዓለም"።

መድኅን እንደ ሕፃናት ጊዜው ሲደርስ ተወለደ፡፡

የተወለደውም ከዓለም አስቀድሞ የነበረ ነው። *(ድጓ)*

## 2. ረቂቅ ጥበቡ የታየበት ነው፡፡

እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ይልቅ ዓለምን ያዳነበት ጥበቡ ረቂቅ መሆኑ የታየው በልደት ነው።

ሰው አምላክ አምላክ ሰው ሆኖ ማየት ድንቅ ጥበብ ነው፡፡

በአንጻሩ ደግሞ የማይሞተው፡፡

በሚሞት *ሥጋ* ተገልጦ

ማየት በአንደበት ከመግለጽ በላይ የሆነ ድንቅ ነገር ነውና፡፡

እግዚአብሔር ሞትንና ሲዖልን ዲያቢሎስን በሥልጣኑ ሳይሆን በሞቱ ድል ይነሳ ዘንድ የአዳምን *ሥጋ* መልበስ መወለድ ነበረበት፡፡

ስለዚህም ነው፡-

‹‹ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ሰው ሆኖ ዓለምን ያዳነበት ጥበ ብ ይበልጣል›› የተባለው።

ሊቁ ጎርጎርዮስ ዘቂሳሪያ በሃይማኖተ አበው እንዲህ ይላል።

"የወልድ ከአብ መወለዱ የማይመረመር ሊናገሩትም የማይችል ነው ። የማይመረመር ረቂቅ ስለሆነ ግዙፉ ረቂቁን መርምሮ ማወቅ የማይቻለው ነው።

ልደቱም እንደሰው ልደት አይደለምና ረቂቅ ምስጢር ነው አይመረመርም"። *(ሃይ. ዘጎር. ምዕ. 13 ክፍ. 1 ቁ. 11-12)*

ነቢየ እግዚአብሔር ሚክያስ "አንቺ ቤተ ልሔም ኤፍራታ አንቺ ከይሁዳ አእላፍ መካከል ትሆኝ ዘንድ ታናሽ ነሽ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ለዘለዓለም የሆነ በእስራኤል ላይ ገዢ የሚሆን ይወጣልና፤" *(ሚክ. 5፥2)* ብሎ የተነበየው ትንቢት ሊቁ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ሲገልጸው በአባታችን በቀዳማዊ አዳም ምክንያት ያጣናትን ልጅነት ሊሰጠን ዳግማዊ አዳም ክርስቶስ የመንግሥተ ሰማያትን የምስጋና ኑሮ በቤተ-ልሔም ገልጧልና ይህች ቤተ ልሔም መንግሥተ ሰማያትን መሰለች ብሎ አመስጥሮታል።

ቤተ ልሔም ከፍ ማለቷ ሊቁም እንዲህ ይገልጣታል።

"ወአንቲኒ በቤተ ልሔም ምድረ ኤፍራታ ኢትቴሐቲ እምነገሥተ ይሁዳ እስመ እምኔኪ ይውጽእ ንጉሥ ዘይርዕዮሙ ለሕዝብየ እስራኤል" እንዲል ቅዱስ ኤፍሬም።

ልደተ ክርስቶስ ከሁሉም የተለየ ነው።

ምክንያቱም ፡-

### 1. ለቀዳማዊ ልደት ደኃራዊ ልደት ማረጋገጫ ምስክር ሆኗል።

ለቀዳማዊ ልደቱ እናት እንዳላስፈለገው ሁሉ ለደኃራዊ ልደቱም አባት ሳያስፈልገው በመለኮታዊ ጥበቡ ከድንግል ተወልዷል።

ልደት ቀዳማዊ ተዐውቀ በደኃራዊ ልደት››
‹‹ያለ እናት ቅድመ ዓለም የተወለደው ልደት፤ በምድር ያለ አ ባት በተወለደው ልደት
ታወቀ ›› እንዲል ቀድሞ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ያለ እናት መወ ለዱን ሊገልጥልን ስለ ወደደ ከእመቤታችን ያለ አባት ተወለደ፡፡

በሥጋ መወሰን  በመለኮት አለመመርመር ለጌታችን ለመድኃ ኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ የሚስማማ  በመሆኑ

"አንተ የማትመረመር ረቂቅ  ነህ ሊረዳህ እና ሊያይህ የሚችል የለም  አንተነትህን የምታውቀው  አንተ ነህ።" *(ቅዳሴ ዮሐንስ)*

## 3. ድኅነተ ዓለም የተረጋገጠበት  ነው፡፡

መድኃኒት ተገኝቷል፤ ሰላምና ዕርቅ ተፈጽሟል፤ ቁራኝነት ተላቋል፤ የሰው ክብር ተመልሷል፤ ጨለማ ተሽሮ በርሃን ወጥቷል፤ ትንቢተ ነቢያት ተረጋግጧል። ነቢዩ  ኢሳይያስ  በትንቢት መነጽር የተመለከተው ተፈጽሟል፡፡

ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤

እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።       *(ኢሳ 7፥14)*

ዓለምን ለማዳን  በግብረ መንፈስ  ቅዱስ ሰው መሆኑ የተረጋ ገጠው ታሕሣሥ 29 ቀን ነው፡፡ ዛቲ ዕለት ዕጽብት ይእቲ።

የእግዚአብሔር  አብ የባህርይ ልጅ የድንግል ልጅ ሆነ።

ረቂቁ ገዘፈ፤ ታየ፤ ተዳሰሰ፤ ተገለጠ፤ ግዙፉ ረቀቀ።

**ማጠቃለያ፡-**

ልደተ እግዚእን ስናከብር ሊዘነጉ የማይገባቸው መሠረታዊ ነገሮች

## 1. ትህትና፤

በዘባነ ኪሩብ በየማነ አብ የሚኖር ማደሪው ዘፋኑ ሁለንተናው እሳት የሆነ በኅሊና ፍጡራን የማይመረመር ራሱን ዝቅ አድርጎ በበረት መወለዱን ፤

## 2. ፍቅር፣

ፍቅር ሰሐቦ ለወልድ ኃያል እመንበሩ /ኃያል ወልድን ፍቅር ከዙፋኑ ሳበው /አወረደው እንዲል፣ እንድሁ እኛን ወዶ መምጣቱን ፣

## 3. ሰላም፣

ለእግዚአብሔር በሰማያት ምስጋና ለምድርም ሰላም ለሰው ዕርቅ እንደ ሆነ፣

## 4. አንድነት፣

መላእክትን ከሰማይ፣ ጠቢባንን ከምሥራቅ፣ እረኞችን ከመንደር፣ እንስሳትን ከበረት፣ በማሰባሰብ በርዕሱ አንድ እንደሆን ገልጦ መለያየትን አስወገዶልናል።

የወሬ ሳይሆን የተግባር ሰዎች እንድንሆን እግዚአብሔር ይርዳን፡፡

**ወንግበር በዓለ በአሐዱ ልብ፣ ወበአሐዱ ምክር፣**

በአንድ ሐሳብና በአንድ ልብ በዓልን እንድርግ /እናክብር/

**ሊቀ ሊቃውንት ዮሴፍ ደሳለኝ**
**በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት**
**የሊቃውንት ጉባኤ አባል**



